አዲስ ዘመን

እፕድ

ማክሰኞ 82ኛ ዓመት ቁጥር 052 ጥቅምት 22 ቀን 2015 ዓ.ም ዋጋ 10.00 ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!



ደርባ ሚድሮክ ሲሚንቶ
ኃ/የተ/የግል ማህበር



በልዩ የደርባ ሲሚንቶ መስመር 8688 ወይም
- 0111 26 26 27 - 0922 11 53 24/26
- 0111 26 26 28 - 0922 72 74 48/49
- 0111 26 26 29 - 0922 72 38 70
- 0111 26 26 30 - 0922 72 38 72
ፋክስ፡- 0111 26 23 45 እና
0111 26 23 18
ይዘዙን
ደረጃቸውን ጠብቀን የምናመርታቸውን ጥራት ያላቸው የሲሚንቶ ምርቶች ቤትዎ ወይም ፕሮጀክትዎ ደጃፍ ላይ ያለውጣ ውረድ በደርባ ትራንስፖርት ኃ.የተ.የግ.ማ አማካይነት እናቀርባለን።
ነገን ዛሬ እንሥራ





# ኮረም፣ ዋጀና ጥሙጋ የኤሌክትሪክ አገልግሎት አገኙ

## - በአላማጣ 42 ትራንስፎርመሮችና 6 ሺህ ሜትር የኤሌክትሪክ መስመር ተቀይሯል

ጌትነት ተስፋማርያም



አዲስ አበባ፡- ኮረም፣ ዋጃና ጥሙጋ አካባቢ የሚገኙ ዜጎች የሙከራ ኤሌክትሪክ አገልግሎት እንዳገኙ የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት አስታወቀ።

በአላማጣና አካባቢው በሕወሓት የሽብር ቡድን ወረራ የተነሳ የወደሙ 42 ዋና ማከፋፈያ ትራንስፎርመሮችና ስድስት ሺህ ሜትር የኤሌክትሪክ ማስተላለፊያ መስመሮች መቀየራቸውን ተናግረዋል።

በኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት የኮርፖሬት ኮሙኒኬሽን ዳይሬክተር አቶ መላኩ ታዬ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በአላማጣ አካባቢ የኤሌክትሪክ አገልግሎት ከተለቀቀ በኋላ በኮረም ዋጃና ጥሙጋ አካባቢዎች በተመሳሳይ ኤሌክትሪክ እንዲያገኙ ጥረት ሲደረግ መቆየቱን አስታውሰዋል።

እንደ አቶ መላኩ ገለጻ፤ አሸባሪው ቡድን ወረራ ወቅት የወደመውን ኤሌክትሪክ መስመር የጥገና ሥራ በመጠናቀቁ በኮረምና ዋጃና ጥሙጋ የሚገኘው ሕብረተሰብ የሙከራ ኤሌክትሪክ አገልግሎት ከዛሬ ጀምሮ እንደሚያገኙ ይጠበቃል።

በኮረምና ዋጃ አካባቢዎች ላይ ጥገና በማከናወን በኤሌክትሪክ ማስተላለፊያ አካባቢዎች ያልታሰበ አደጋ እንዳይደርስ ሙሉ መስመሩ ላይ የፍተሻ ስራ ሲከናወን መቆየቱን ተናግረዋል።

በተመሳሳይ በሌሎች የሰሜን ኢትዮጵያ አካባቢዎችም በሽብር ቡድኑ የወደሙ የኤሌክትሪክ መሰረተ ልማቶችን የመጠገን ስራው እንደቀጠለ መሆኑን አቶ መላኩ ጠቁመዋል።

ከአሸባሪው ቡድን ነፃ በወጡ አካባቢዎች የኤሌክትሪክ መሰረተ ልማት ጥገና ለማከናወን አስቀድሞ

ኮረም፣ ዋጃና ጥሙጋ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል



# «የምርት ስወራ ችግሮችን ለመግታት በአስመጪዎችና አከፋፋዮች ላይ ጥብቅ ቁጥጥር ማድረግ ያስፈልጋል»

- አቶ ክቡር ገና
የምጣኔ ሀብት ባለሙያ

ጌትነት ተስፋማርያም

አዲስ አበባ፡- የኑሮ ውድነቱን እያባባሰ ያለውን የምርት ስወራ ችግር ለመግታት አስመጪዎችና አከፋፋዮችን በውል በመለየት ጥብቅ ቁጥጥር ማድረግ እንደሚያስፈልግ የምጣኔ ሀብት ባለሙያው አቶ ክቡር ገና አመለከቱ። የምርት ስወራን ከመከላከል ጎን ለጎን ምርትና ምርታማነትን ማሳደግ እንደሚገባም ገልጸዋል።

አቶ ክቡር ገና ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት በሰጡት አስተያየት፤ የዋጋ ግሽበቱ፣ የወጣቱ ስራ አጥ ቁጥር፣ የኑሮው መዛባት እና ተያያዥ ችግሮች ዜጎችን ወደ ግጭት እንዲያመሩ ሊገፋፋ እንደሚችል አምራችና አቅራቢው ሊገነዘብ ይገባል።

በዓለም ደረጃ ያለው የኢኮኖሚ መቀዛቀዝ፤ በተጨማሪ በሰሜን ኢትዮጵያ የተከሰተው ጦርነት ኢኮኖሚያችን ላይ ተጽዕኖ አሳድሯል። እነዚህና ተያያዥ ምክንያቶች ባሉበት ፍላጎት ሲጨምር ምርትም በአግባቡ

«የምርት ስወራ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል



# «ኢትዮጵያ ሉዓላዊነቷን እና የሕዝቦቿን ሰላም የማስጠበቅ ሃላፊነት አለባት»

- አምባሳደር እሸቴ ጥላሁን
በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር
የአሜሪካ እና አውሮፓ ጉዳዮች
ዳይሬክቶሬት ጀኔራል

ዘላለም ግዛው

አዲስ አበባ፡- ኢትዮጵያ ሉዓላዊነቷን፣ የግዛት አንድነቷን እና የሕዝቦቿን ሰላም የማስጠበቅ ሃላፊነት ስላለባት ይህንኑ ትቀጥላለች ሲሉ በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር

«ኢትዮጵያ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል



ፎቶ - ሳሙኤል ተስፋዬ

# ኢፕድ የጀመራቸው አዳዲስ አሰራሮች ተጠናክረው እንዲቀጥሉ ቋሚ ኮሚቴው አሳሰበ

ጀማል ታመነ

አዲስ አበባ፡- የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት የጀመራቸውን አዳዲስ አሠራሮች አጠናክሮ እንዲቀጥል በሕዝብ ተወካዮች ምክርቤት የሕግ፣ ፍትህና ዴሞክራሲ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ አሳሰበ። ቋሚ ኮሚቴው የድርጅቱን የ2015 ዓ.ም እቅድና የ2015 ዓ.ም ሩብ ዓመት እቅድ አፈጻጸም ሪፖርት አዳምጧል።

የድርጅቱን እቅድና የእቅድ አፈጻጸም ሪፖርት ያቀረቡት የኢፕድ ዋና ሥራ አስፈጻሚ አቶ ጌትነት ታደሠ በዚህ ወቅት እንደገለጹት፤ ድርጅቱ ከ2011 ጀምሮ በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በጸደቀለት አዋጅ ቁጥር 1151/11 መሰረት ተቋማዊ ማሻሻያዎችን እያደረገ መጥቷል።

ኢፕድ የጀመራቸው... ወደ ገጽ 4 ዞሯል








«ከውጭ ሃይሎች እየሰማን ያለነው የሰላም መልዕክት ሳይሆን ተከታታይ ማስጠንቀቂያዎችን ነው»

- አምባሳደር ታዬ አጽቀሥላሴ

ገጽ 3

# በሩብ ዓመቱ ከ1600 በላይ የሳይበር ጥቃት ሙከራዎች ተደርገዋል

**ዳግማዊት ግርማ**

አዲስ አበባ፡- በ2015 በጀት ዓመት የመጀመሪያ ሩብ ዓመት ብቻ ከ1600 በላይ የሳይበር ጥቃት ሙከራዎች በኢትዮጵያ ላይ መሞከራቸውን የኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት አስተዳደር አሳወቀ። ዓለማችን ባሳለፍነው የፈረንጆቹ ዓመት ብቻ በሳይበር ጥቃት ከ5 ነጥብ 8 ትሪሊዮን ዶላር በላይ ተመዝብራለችም ነው የተባለው።

በትናንትናው "የህዝብ ተወካዮችና ፌዴሬሽን ምክርቤት አባላት ሀገራዊ የሳይበር ደህንነትና የሳይበር ደህንነትን በማስጠበቅ ረገድ ያላቸው ሚና" በሚል በተከወነ የምክክር መድረክ ዋና ዳይሬክተሩ አቶ ሰለሞን ሶካ በ2015 በጀት ዓመት የመጀመሪያ ሩብ ዓመት ብቻ ከ1600 በላይ የሳይበር ጥቃት ሙከራዎች በኢትዮጵያ ላይ መሞከራቸውን ገልጸዋል።

የቴክኖሎጂ ጥገኝነት እና ዝቅተኛ የሳይበር ደህንነት የግንዛቤ ደረጃ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ ለመጣው የሳይበር ጥቃት ዋነኛ መንስኤ እንደሆነ የገለጹት ዋና ዳይሬክተሩ፤ ይህንን ከመከላከል አንጻር የሕብረተሰቡን ብሎም የተቋማትን የሳይበር ደህንነት የግንዛቤ ደረጃ ቀጣይነት ባለው መልኩ ማሳደግ እንደሚገባ ገልጸዋል።

በ2015 በጀት ዓመት የመጀመሪያ ሩብ ዓመት በሀገራችን የተቃጡ የሳይበር ጥቃት ሙከራዎቹ ዋነኛው ትኩረታቸው ስትራቴጂካዊ ጠቀሜታቸው ላቅ ባሉ ተቋማት ውስጥ መደረጋቸውን ዋና ዳይሬክተሩ ገልጸዋል።

እንደ ዋና ዳይሬክተሩ ገለፃ፤ ጥቃቶቹ ሆስፒታሎች፣ የትምህርት፣ የሃይል ማመንጫና ማሰራጫ ተቋማት፣ የፋይናንስ፣ የመከላከያና ደህንነት ተቋማት፣ የቴሌኮም መሰረተ ልማቶች እና የአየር ትራፊክ ቁጥጥር ሥርዓቶች ላይ ኢላማ ያደረጉ ናቸው።

መስሪያቤታቸው በሃገራችን ክልከላ ባለባቸውና አቅም ባልተፈጠረባቸው የሳይበር ቴክኖሎጂ ምርቶች ላይ አቅም እየፈጠረ መሆኑን ያመላከቱት ዋና ዳይሬክተሩ፤ ያለ ዜጎች የሳይበር ደህንነት ግንዛቤ እድገት በቴክኖሎጂ ባለቤትነት ብቻ የሀገራችንን የሳይበር ሉዓላዊነት ማስጠበቅ አይቻልም ሲሉም ገልጸዋል።

የዘርፉ ተመራማሪዎች የሀገራችንን የሳይበር ሉዓላዊነት ለማረጋገጥ የእያንዳንዱ ዜጋ ሚና ከፍተኛ መሆኑን በመገንዘብ በዘርፉ ላይ ያለውን የግንዛቤ ክፍተት ለመሙላት የበኩላቸውን እንዲወጡም ዋና ዳይሬክተሩ አሳስበዋል።

የሳይበር ጥቃት ከዓለማችን ቀዳሚ አስር ቀውሶች ውስጥ የአየርንብረት ቀውስን ተከትሎ በሁለተኝነት የሚታይ ነው ያሉት አቶ ሰለሞን፤ በዓለማችን የደረሰው ጥቃት መጠን ከባለፈው ሩብ ዓመት 28 በመቶ ጭማሪ ማሳየቱንም ነው ያመላከቱት።

ዓለማችን ባሳለፍነው የፈረንጆቹ ዓመት ብቻ በሳይበር ጥቃት ከአምስት ነጥብ ስምንት ትሪሊዮን ዶላር በላይ ተመዝብራለችም ሲሉ ዋና ዳይሬክተሩ ገልጸዋል።

የፌደሬሽን ምክርቤት አፈጉባኤው አቶ አገኘሁ ተሻገር በበኩላቸው፤ መንግሥት ለዘርፉ ልዩ ትኩረት በመስጠት እየሰራ መሆኑን በመግለጽ ሀገራችን በዘርፉ ተወዳዳሪ እንድትሆን ሁሉም ባለድርሻ አካላት ድርሻቸውን ሊወጡ ይገባል ብለዋል።

በዓለም ለ19ኛ እንዲሁም በኢትዮጵያ ለሶስተኛ ጊዜ "የተቀናጀ የሳይበር ደህንነት ለሀገር ሉዓላዊነት" በሚል የሚከበረው የሳይበር ደህንነት ወር ከጥቅምት አንድ እስከ 30 ድረስ በተለያዩ የሳይበር ደህንነት የግንዛቤ ማስጨበጫ ተግባራት እየተከበረ እንደሚገኝ ይታወቃል።



# በከተማና በገጠር መካከል ተመጋጋቢ እድገት ለመፍጠር የክልሎች ስፓሻል ፕላን እየተዘጋጀ ነው

**ዳንኤል ዘነበ**

አዲስ አበባ፡- በከተማና በገጠር መካከል ተመጋጋቢ የሆነ እድገት መፍጠር የሚያስችል የክልሎች ስፓሻል ፕላን እየተዘጋጀ እንደሆነ ተገለጸ።

በተባበሩት መንግሥታት ሃቢታት የከተማ ኢኮኖሚ አማካሪ ዶክተር በላይ ፊሌ እንዳሉት፤ በከተማና በገጠር መካከል ተመጋጋቢ የሆነ እድገት መፍጠር የሚያስችለው ስፓሻል ፕላን በ10 ክልሎች እየተዘጋጀ ነው። ከሀገራዊ ስፓሻል ፕላንና ከከተሞች መዋቅራዊ ፕላን ጋር ተቀናጅቶ የሚተገበርና ለቀጣይ 20 ዓመት ከተሞች የሚመሩበት እቅድ ሲሆን ፤ የክልሎች ስፓሻል ፕላኑ ተዘጋጅቶ ተግባራዊ ሲደረግ በከተማና በገጠር መካከል ተመጋጋቢ የሆነ እድገት ይፈጥራል ብለዋል።

ክልሎች ስፓሻል ፕላን ስለሌላቸው የከተሞችና የገጠሩ እድገት ተመጋጋቢነት እንደሌለው አመልክተው፤ በ10 ክልሎች እየተዘጋጀ የሚገኘው የክልሎች ስፓሻል ፕላን ተግባራዊ ሲደረግ በከተማና በገጠሩ መካከል ተመጋጋቢ የሆነ እድገት መፍጠር እንዲሚቻልም ተናግረዋል ።

እንደ ዶክተር በላይ ገለጻ፤ "ከዚህ በተጨማሪም በክልሎች ስፓሻል ፕላኑ መዘጋጀቱ ክልሎችን ከሌሎች ክልሎች፣ ከተሞችን እርስ በእርስና ከገጠሩ ጋር በማስተሳሰር ዘላቂ እድገት ለማምጣት ያስችላል። ከተሞች እንዴት ማደግና የት መመስረት እንዳለባቸው አቅጣጫ ያሳያል።

እቅዱ የከተሞችን መሬት ለቱሪዝም፣ ለኢንዱስትሪ፣ ለመሰረተ ልማት፣ ለንግድ፣ ለአገልግሎትና መሰል ዘርፎች በትክክል ለመጠቀምና ከተሞች በኢኮኖሚ በዘላቂነት እንዲያድጉ ያደርጋቸዋል "ሲሉም ገልጸዋል።

የከተማና መሠረተ ልማት ሚኒስትር ዴኤታ አቶ ፈንታ ደጀን በበኩላቸው ፤ ሀገራዊ ስፓሻል ፕላንና የከተሞች መዋቅራዊ ፕላን ቢዘጋጅም ፤ በክልሎች ስፓሻል ፕላን ባለመኖሩ ምክንያት ሁለቱን አቀናጅቶ ለመጠቀም አለመቻሉን አስታውቀዋል።

የክልሎች ስፓሻል ፕላን የማዘጋጀት ኃላፊነት የክልሎች መሆኑን የጠቀሱት አቶ ፈንታ ፤ ክልሎቹ ካላቸው የፋይናንስ አቅም አኳያ ለማዘጋጀት አለመቻላቸውን አስረድተዋል ። "ሚኒስቴሩ ይሄን መሠረት በማድረግ ከተባበሩት መንግሥታት ሃቢታት ጋር በመሆን ከዓለም ባንክ ባገኘው የገንዘብ ድጋፍ የክልሎች ስፓሻል ፕላንን የማዘጋጀት ሂደት ፕሮጀክት ተግባራዊ ሊደረግ ችሏል ብለዋል።

የክልሎች ስፓሻል ፕላን ፕሮጀክትን ከዳር ለማድረስ አስፈላጊው ጥረት እየተደረገ መሆኑን የጠቆሙት ሚኒስትር ዴኤታው ፤ በተመድ ሃቢታት በኩል ለክልሎች የተበረከቱት 10 ተሸከርካሪዎች እንደማሳያ አንስተዋል ። ክልሎችም ተሸከርካሪዎቹን ለታለመላቸው ዓላማ ብቻ እንዲጠቀሙም አሳስበዋል።

የክልሎች ስፓሻል ፕላን ከዓለም ባንክ በተገኘ 7 ነጥብ 2 ሚሊዮን ዶላር በሃረሪ ፣ አፋር ፣ ኦሮሚያ፣ አማራ ፣ በደቡብ ፣ ደቡብ ምዕራብ ፣ ሲዳማ ፣ ጋምቤላ ፣ ቤኒሻንጉል ክሎች ተግባራዊ እየተደረገ የሚገኝ ፕሮጀክት እንደሆነ ተገልጿል።

# ቦርዱ የሂሳብ አያያዝና ሪፖርት አቀራረብ መስፈርቶችን የሚያስተገብር ፍኖተ-ካርታ አዘጋጀ

**ሙሳ ሙሐመድ**

አዲስ አበባ፡- ዓለም አቀፍ የሂሳብ አያያዝና ሪፖርት አቀራረብ መስፈርቶችን መተግበር የሚያስችል ፍኖተ-ካርታ ማዘጋጀቱን የኢትዮጵያ ኦዲት ቦርድ አስታወቀ።

የኢትዮጵያ ኢዲት ቦርድ ዋና ዳይሬክተር ወይዘሮ ሒክመት አብዱላሂ እንደተናገሩት፣ ዓለም አቀፍ የሂሳብ አያያዝና ሪፖርት አቀራረብ መስፈርቶችን ተከትሎ የሂሳብ አያያዝና ሪፖርት አቀራረብን በኢትዮጵያ ለመተግበር የሚያስችል ፍኖተ-ካርታ ተዘጋጅቷል።

እንደ ወይዘሮ ሒክመት ማብራሪያ፣ ቦርዱ ከፋይናንስ ጋር የተገናኙ ገቢራትን የሚያከናውኑ ተቋማት የዓለም አቀፍ የሂሳብ አያያዝ እና ሪፖርት አቀራረብ መስፈርቶችን የተከተሉ እንዲሆኑ ለማስቻል ፍኖተ-ካርታውን አዘጋጅቷል።

በፍኖተ-ካርታው የኢትዮጵያ ሂሳብ አያያዝና ሪፖርት አቀራረብ ሒደቶች የዓለም አቀፉን መስፈርቶች ተከትለው እንዲተገብሩ የሚያስችል ነው። የዚህ ፍኖተ-ካርታም ትግበራም እስከ ሐምሌ 2015 ዓ.ም ድረስ ተራዝሟል።

የተዘጋጀው ፍኖተ-ካርታም የሂሳብ አቅራቢዎችን በሶስት ከፋፍሎ ተግባራዊ እንደሚያደርግ ወይዘሮ



**ወይዘሮ ሒክመት አብዱላሂ**

ሒክመት አክለው ተናግረዋል።

ወይዘሮ ሒክመት ሶስቱን የሒሳብ አቅራቢዎች ክፍፍል ሲተነትኑ፣ የዓለም አቀፍ የሂሳብ አያያዝና ሪፖርት አቀራረብ መስፈርቶችን ለመተግበር የሰለጠኑ ባለሙያዎች እጥረት መኖርን ታሳቢ ያደረገ ነው፣

ሌላኛው ደግሞ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የአካውንቲንግ ትምህርት አሰጣጥ፣ የዓለም አቀፍ የሂሳብ አያያዝና ሪፖርት አቀራረብ መስፈርቶች ሥልጠና ጋር የተያያዙ ችግሮች መኖር እና በሀገር ደረጃ የተመሰከረላቸው እና እውቅና የተሰጣቸው የንብረት እና ገማቾች እጥረት መኖሩ ይገኙበታል ብለዋል።

የፋይናንስ አስፈጻሚዎች በወቅታዊና ተገቢነት ባላቸው ጉዳዮች ላይ ግንዛቤያቸውን እንዲያሰፉ የሚያስችል የውይይት ብሎም የትብብርና ትውውቅ መድረክ በቀጣይነት እንደሚዘጋጅም ጠቁመዋል።

በኢትዮጵያ ከፋይናንስ ጋር የተያያዙ አሳሳቢ ችግሮች መኖራቸውን የጠቀሱት ወይዘሮ ሒክመት፣ ችገሮቹን ለመቅረፍ ውጤት-ተኮርና ገቢራዊ የሆነ መፍትሄ እንዲመጣ የፋይናንስ ባለሙያዎች እና ሌሎችም ጉዳዩ የሚመለከታቸው ተቋማት ተገናኝተው የሚመክሩበት መድረክ በየጊዜ ያስፈልጋቸዋል ብለዋል።

የምክክር መድረኮቹም በየወቅቱ የፋይናንስ ባለሙያዎቹ የሚያቀርቧቸው ምክረ ሃሳቦችም ተፅዕኖ ፈጣሪና ተቀባይነት ያላቸው መሆን እንዳለባቸውም መክረዋል።

# ጥቅምት 24 ቀን «መቼም አንረሳውም» በሚል መሪ ቃል በመላው ሀገሪቱ ታስቦ ይውላል

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አዲስ አበባ፡- መከላከያ ሠራዊት ጥቃት የደረሰበትን ቀን ምክንያት በማድረግ ጥቅምት 24 ቀን 2015 ዓ.ም ‘መቼም አንረሳውም’ በሚል መሪ ቃል በመላው ሀገሪቱ ታስቦ እንደሚውል የመንግሥት ኮሙኒኬሽን አገልግሎት ሚኒስትር ዴኤታ አቶ ከበደ ደሲሳ ተናገሩ።

የመንግሥት ኮሙኒኬሽን አገልግሎት ትናንትና በወቅታዊ ጉዳዮች ላይ በሰጠው መግለጫ፤ ጥቅምት 24 ቀን 2013 ዓ.ም በሰሜን ዕዝ ላይ የተፈጸመውን ግፍ በማሰብ የፊታችን ጥቅምት 24 ቀን “መቼም አንረሳውም” በሚል መሪ ቃል ታስቦ ይውላል ብለዋል።

የትግራይ ክልልን ሲጠብቁ የነበሩ በርካታ ቁጥር ያላቸው የሀገር መከላከያ ሠራዊት አባላት በአሸባሪው ሕወሓት ጭካኔ በተሞላበት ድርጊት ጥቅምት 24 ቀን በግፍ መገደላቸውን አስታውሰው፤ መከላከያ ሠራዊት ላይ የተፈጸመውን ግፍ በማሰብ ጥቅምት 24 ቀን በዕለቱ የተለያዩ ሁነቶች እንደሚከናወኑ አቶ ከበደ ገልጸዋል።

እንደ ሚኒስትር ዴኤታው ገለጻ፤ በዕለቱ ማለዳ አራት ሰዓት ላይ ተማሪዎች፣ አሽከርካሪዎችንና የፀጥታ ኃይል አባላትን ጨምሮ የተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎች ዕለቱን የሚያስቡበት ሁነት ታቅዷል።

የፊታችን ጥቅምት 24 ቀን ኢትዮጵያውያን በያሉበት ለአንድ ደቂቃ ያክል ቆመው ለሀገር መከላከያ ሠራዊት ያላቸውን አጋርነት እንደሚያሳዩም አቶ ከበደ ገልጸዋል።

ሚኒስትር ዴኤታው እንዳስታወቁት፤ ተግባሩ መቼውንም ቢሆን የማይረሳ የሀገር ክህደት ወንጀል ሆኖ በታሪካችን ሲነሳ የሚኖር ይሆናል።



አቶ ከበደ ደሲሳ


የሁለተኛው መታሰቢያ ዓመት ጥቅምት 24 ቀን 2015 ዓ.ም በመላ ሀገሪቱ በሁሉም የመንግሥትና የግል ተቋማት እንዲሁም በየክልል ዕርከን በሚገኙ የመንግሥት ተቋማትም ታስቦ እንደሚውል ጠቁመዋል።

ዕለቱ የሀገር መከላከያ ሠራዊት በሸብር ቡድኑ ስለደረሰበት ግፍና እየከፈለ ስላለው ዋጋ የሚያስቡ ተጨማሪ ሁነቶችና የተለያዩ መርሀ ግብሮች እንደሚከናወኑም አቶ ከበደ ገልጸዋል።

የሀገር መከላከያ ሠራዊትን ተጋድሎ ለማሰብ በተዘጋጁ መርሀግብሮችም ሁሉም ኢትዮጵያዊ በንቃት እንዲሳተፍም የመንግሥት ኮሙኒኬሽን አገልግሎት ሚኒስትር ዲኤታው ጥሪ አቅርበዋል።

# ጥናቱ ወደ አራተኛው የኢንዱስትሪ አብዮት የሚደረገውን ጉዞ ያግዛል

**ገመቹ ከድር**



አዲስ አበባ፡- ጥናቱ ገበያው የሚፈልገውን የሰዉ ኃይል ፍላጎትና አቅርቦትን በማጣጣም ወደአራተኛዉ ኢንዱስትሪ አብዮት የሚደረገውን ሽግግር እንደሚያግዝ የኢትዮጵያ ፖሊሲ ጥናት ኢንስቲትዩት አስታወቀ። ኢንስቲትዩቱ ያካሄዳቸውን ምርምርና ጥናት ውጤቶች ከበላድርሻ አካላት ጋር ተወያይቶበታል።

የኢትዮጵያ ፖሊሲ ጥናት ኢንስቲትዩት ዋና ዳይሬክተር ፕሮፌሰር በየነ ጴጥሮስ እንደገለጹት፤ ኢኒስቲትዩቱ የምርምርና ጥናት ስራዎች ውጤት ለባለድርሻ አካላት በማቅረብ ጠቃሚ ግብዓቶችን ለማስገኘት እየሰራ ይገኛል።

እንደ ሀገር ስራ አጥ ለሆነው ወጣት መንግሥት መፍትሄ ለመፈለግ በቁርጠኝነት በመንቀሳቀስ ላይ እንደሚገኝ ጠቅሰው ችግሩን በጥናትና ምርምር በመዳሰስ መፍትሄ ለመፈለግ እየተሰራ መሆኑን ገልጸዋል።

እንደ ፕሮፌሰር በየነ ገለጻ ምርምሩና ጥናቱ በስራ ላይ ያለው ፖሊስና ስትራቴጂዎች ከወቅቱ ጋር በማገናዘብ ማሻሻያዎችን ማቅረብና አዳዲስ የፖሊሲ ምክረ ሃሳቦችን ለማፍለቅ ያግዛል።

በአዲሱ አደረጃጀት ኢንስቲትዩቱ በስድስት ጥናትና ምርምር ማእከሎች እና 14 የምርምር ክፍሎች ስራውን በመስራት ላይ ይገኛል ያሉት ፕሮፌሰር በየነ ከእነዚህም አንዱ ኢንዱስትሪ ልማት ፖሊሲ ጥናት ነው ብለዋል።

ስራ አጥነትን ለመቀነስ በዝቅተኛ ደረጃ ሙያ ክህሎት በጊዜያዊ ስራ ላይ የሚገኙ ወጣቶችን ለማሻሻል ጥራት ያለው ትምህርትና ሥልጠና ማቅረብ ወሳኝ ነው። አሁን እየተሰጠ ካለው ትምህርትና ሥልጠና አሁን ካለው ገበያ ፍላጎት ጋር ያለውን መስተጋብሮች በማጥናት የፖሊስና ሲትራቴጂ ምክረ ሃሳቦች መቅረቡን ገልጸው በጥናት የቀረቡ ተግዳሮቶችና ፖሊሲ ምክረ ሃሳቦች በስራ ክህሎት ሚኒስቴርና በሚመለከታቸው ተቋማት ዳብሮ የተፈለገውን ውጤት ለማስገኘት አጋዥ እንደሚሆን እምነታቸው መሆኑን ገልጸዋል።

የሥራ ክህሎት ሚኒስትር ዴኤታ አቶ ንጉሱ ጥላሁን በዚሁ ጊዜ እንደተናገሩት ፤ ተጠንቶ የቀረበው ጥናት ገበያ ላይ ያሉትን ክፍተቶች በመለየት ማህበራዊ ኢኮኖሚያዊ ችግሮችን በመፍታት ወደ አራተኛው ኢንዱስትሪ የሚደረገውን ጉዞ እውን የሚያደርግ ነው። ክፍተቶች በመለየት መፍትሄዎች ሊሆኑ የሚችሉ መነሻ ሃሳቦች ለቀጣይ ፖሊሲ አቅጣጫዎች ግብዓት እንደሚሆን ገልጸዋል።

በኢንስቲትዩቱ የፖሊሲ ተማራማሪና ጥናት ቡድን ወክለው የጥናቱን መነሻ ሃሳቦች ያቀረቡት ዶክተር አማረ ማተቡ በኢንስቲትዩቱ የቀረበው ጥናት ለወጣቶች ስራ እድል ክህሎት በመጨመር ከአራተኛው ኢንዱስትሪ አብዮት ጋር ለማስተሳሰር ያግዛል። ህብረተሰቡን ለመቅረጽና ኢኮኖሚያዊ ሽግግር እውን ለማድረግ ትምህርትና ሥልጠና ላይ ትኩረት እንዳደረገ ገልጸዋል።

# «ከውጭ ሃይሎች እየሰማን ያለነው የሰላም መልዕክት ሳይሆን ተከታታይ ማስጠንቀቂያዎችን ነው»

**- አምባሳደር ታዬ አጽቀሥላሴ**

**በኃይሉ አበራ**

አዲስ አበባ፡- ኢትዮጵያ ከሊግ ኦፍ ኔሽን ጀምሮ እስከ የተባበሩት መንግሥታት ቀዳሚ አባል ሀገር የሆነችና ሉዓላዊነቷን አስጠብቃ የኖረች ነጻ አገር ብትሆንም ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ይህንን ነጻነቷን እና ሉዓላዊነቷን በሚፈታተን መልኩ ከአንዳንድ የውጭ ሃይሎች ማስፈራሪያና ማስጠንቀቂያዎች እየደረሰባት መሆኑን አምባሳደር ታዬ አጽቀስላሴ ገለጹ።

አምባሳደር ታዬ አጽቀሥላሴ በሰሞኑ በተደረገው በመንግሥታቱ ድርጅት ሶስተኛ ኮሚቴ 77ኛ ጉባኤ ላይ እንደገለጹት፤ ኢትዮጵያውያን ውስጣዊ አንድነታቸውን አስጠብቀው የቆዩ መሆኑና ከራሷ አልፋ ለአፍሪካውያን አንድነት ጉልህ ድርሻ እንዳላት ታሪክ ይመሰክራል። ሆኖም በሰሜኑ የአገራችን ክፍል ከተከሰተው ጦርነት ጋር ተያይዞ በኢትዮጵያ የውስጥ ጉዳይ በመግባት ጭምር ተደጋጋሚ ጫና ሲደርስባት ይታያል።

አምባሳደር ታዬ እንዳሉት፤ ሰሞኑን ከአንዳንድ ምዕራባውያን እየሰማን ያለነው የሰላም መልዕክት ሳይሆን ተከታታይ ማስጠንቀቂያዎችን ነው፤ እንደምንረዳው መተማመን ሞቷል፤ በግራም በቀኝም አለመተማመን እየበዛ ነው።




ነገር ግን በርካታ ፈተናዎችን ማለፍ የቻለች ኩሩ አፍሪካዊት ሀገር መሆኗን ማመን አለብን ብለዋል።

ዛሬም የሚገጥሙንን ፈተናዎች በእርግጠኝነት እንደምንሻገር ለመንግሥታቱ ድርጅት አባል አገራት ለማስታወስ እወዳለሁ ሲሉም አሳስበዋል።

በአንዳንድ ኃያላን ሀገሮች ዐይን ፊት በሁለተኛው የዓለም ጦርነት ወቅት እንደሆነው ኢትዮጵያውያን አቅመቢስ መስለን እንታይ ይሆናል ያሉት አምባሳደር ታዬ አጽቀሥላሴ እንዳሉት፣ የውስጣችን መንፈስ ጽኑ ነው፤ የውስጣዊ መንፈሳችን ጥንካሬ ኢትዮጵያዊ ሆኖ ለመቆም ብቻ ሳይሆን ሰላማዊ ለመሆን እና ተግዳሮቶቻችንን ለመፍታት ጭምር ነው።

በንግግራቸውም ዛሬም የ120 ሚሊዮን ሕዝባችንን እጣ ለውስን ኤክስፐርቶች አንተውም፤ ነገር ግን ይህን ስል ሁልጊዜም መልካም እይታና አስተሳሰብ ላላቸው በራችን ክፍት ነው፤ ይሁንና በመኮነንና በማውገዝ እኛን ለሞት አሳልፈው ሊሰጡን ቀድመው የወሰኑትን የሚያደርጉትን አያውቁምና ይቅር ልንላቸው ይገባል ብለዋል።

አምባሳደር ታዬ በንግግራቸውም ሁሉም የሰብዓዊ መብት ጥሰት ላይ የተሳተፉ አካላት ተጠያቂ መሆናቸውን እንደ መንግሥት ላረጋግጥላችሁ እችላለሁ ብለዋል። ዘላቂ ሰላም ሊረጋገጥ የሚችለውም በሁሉም ክልሎች የተፈጸሙት ወንጀሎች ላይ ፍትሃዊነት እና ተጠያቂነት ሲኖር በመሆኑ የማንም ጣልቃ ገብነት ሳያስፈልገው በራሳችን የምንሰራው እንደሆነም አመላክተዋል።

# የኢትዮጵያ ልማት ባንክ ለጀማሪ የፈጠራ ባለቤቶች አራት ቢሊዮን ብር መደበ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አዲስ አበባ፡- የኢትዮጵያ ልማት ባንክ ጀማሪ የፈጠራ ባለቤቶችን ለመደገፍ አራት ቢሊዮን ብር መመደቡን አስታወቀ።

የኢትዮጵያ ልማት ባንክ ፕሬዚዳንት ዮሃንስ አያሌው እንደገለጹት፤ ባንኩ የፈጠራ ባለቤቶችን ለመደገፍ አራት ቢሊዮን ብር የመደበ ሲሆን የባንኩን ድጋፍ የሚሹ ስራ ፈጣሪዎች በስፋት ከመጡ በጀቱን ከዚህም በላይ ከፍ ያደርጋል።

እስካሁን ባለው በግብርናው ዘርፍ የመጡ የፈጠራ ሃሳቦች የአዋጭነት ጥናት አጥንተው የቢዝነስ እቅድ እንዲያቀርቡ እንደተነገራቸውም ነው የገለጹት።

በዲጂታል ኢትዮጵያ 2025 ስትራቴጂ ትኩረት ከተሰጣቸው ጉዳዮች አንዱ የግል ዘርፉ በዲጂታል ኢኮኖሚው መሳተፍ የሚያስችል ምቹ ሁኔታን መፍጠር እንደሆነም አስረድተዋል።

ባንኩ ስራ ፈጣሪዎችን ለመደገፍ አዲስ ሃሳብ ይዞ የሚመጣ ስራ ፈጣሪ ፈጠራው የራሱ መሆኑ ከተረጋገጠ በኋላ የፈጠራ ሃሳቡ አዋጭ መሆኑን በማጥናት ወጪውን ሸፍኖ ሃሳቡ ወደ ስራ እንዲቀየር ድጋፍ እንደሚያደርግም ነው የገለጹት።

ስራ ፈጣሪ ወጣቶች በበኩላቸው ፤ የፋይናንስ ተቋማት ለሀገር የሚጠቅሙ አዳዲስ የፈጠራ ሃሳቦችን እውን ለማድረግ በቂ ድጋፍ ማድረግ አለባቸው ብለዋል።

እንደ ሀገር ጀማሪ የፈጠራ ሃሳብ ባለቤቶች ከሚገጥሟቸው ችግሮች አንዱና ዋነኛው የገንዘብ እጥረት መሆኑን ያነሳሉ። የሀገርና የማህበረሰብ ችግሮችን መነሻ በማድረግ መፍትሔ ይዘው የሚመጡ የፈጠራ ሃሳቦች ሀገርን ስለሚጠቅሙ በቂ ትኩረት ሊሰጣቸው ይገባል ማለታቸውን ኢዜአ ዘግቧል።

የፈጠራ ሃሳብ ባለቤቶች ስራቸውን ወደ ተግባር እንዳይቀይሩ ማነቆ የሆነባቸውን የገንዘብ አቅርቦት ለመፍታት የፋይናንስ ተቋማት ድጋፍ ወሳኝ መሆኑ ታውቋል።

# ኮረም፣ ዋጃና ጥሙጋ...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

ዝግጅት ተደርጎ እንደነበር ያስታወሱት አቶ መላኩ፤ ወራሪው ኃይል በለቀቃቸው አካባቢዎች እግር በእግር እየተከተሉ በአስቸጋሪ ሁኔታዎች ውስጥም የመሰረተ ልማት ጥገናው እየተከናወነ መሆኑን ገልጸዋል።

በጋራ ጥረት በተከናወነ ስራ ከአላማጣ ቆቦ የተዘረጋውንና ውድመት የደረሰበትን የኤሌክትሪክ መስመር መጠገኑን አስታውሰው፤ የኤሌክትሪክ መሰረተ-ልማት ጥገናው በአጭር ጊዜ ለማጠናቀቅ 120 ሠራተኞች ቀንና ማታ በከፍተኛ ትጋት ስራውን ማከናወናቸውን አቶ መላኩ ተናግረዋል።

በጥገና ስራው በአላማጣና አካባቢ የሚገኙና በአሸባሪው ሕወሓት ቡድን ወረራ የተነሳ የወደሙ 42 ዋና ማከፋፈያ ትራንስፎርመሮች መቀየራቸውን ገልጸዋል።

ከዚህ ባለፈ በጥይት ጭምር ተመተው የወደሙ የኤሌክትሪክ ማስተላለፊያ መስመሮች መኖራቸውን ጠቁመው፤ ጉዳት የደረሰበትን ስድስት ሺህ ሜትር የኤሌክትሪክ ማስተላለፊያ መስመር መቀየሩን አስታውቀዋል።

የተቋሙ ሰራተኞች በአስቸጋሪ መልከአ ምድርና የአየር ንብረት 24 ሰዓት መስራታቸውን የተናገሩት አቶ መላኩ፤ ከሰራተኞቹ ባለፈ የአካባቢው አስተዳደር፣ የጸጥታ አካላትና ህብረተሰቡ ላደረጉ ትብብር ምስጋና አቅርበዋል።

ከአላማጣ እስከ ቆቦ ከተከናወነው የጥገና ስራ ባለፈ ከአላማጣ እስከ ላሊበላ የተዘረጋው የ66 ኪሎ ቮልት የትራንስሚሽን መስመር የጥገና ሥራ ከ90 በመቶ በላይ መከናወኑን ገልጸዋል።

ህብረተሰቡ የኤሌክትሪክ አገልግሎት እንዲያገኝ ለማድረግ ሠራተኞች አሁንም ሌት ተቀን ጥረት እየተደረገ መሆኑን ጠቁመዋል።

ከጥገና ስራው ባለፈ በቆቦና ሮቢት ከተሞች ላይ የነበሩ የኤሌክትሪክ አገልግሎት መስጫ ማዕከላት ሙሉ በሙሉ በሽብር ቡድኑ መዘረፋቸውን ገልጸው፤ አጠቃላይ የጉዳት መጠኑም በቀጣይ ጊዜያት ተጠንቶ ይፋ እንደሚደረግ ገልጸዋል።

በአሸባሪው የሕወሃት ቡድን በፈጸመው ወረራ በአማራና አፋር ክልልና ትግራይ አካባቢዎች የኤሌክትሪክ መሰረተ ልማት ላይ በተደጋጋሚ ጉዳት አድርሷል።

# ኢፕድ የጀመራቸው...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

ድርጅቱ የ10 ዓመት ስትራቴጅካዊ ዕቅድ አዘጋጅቶ ወደ ተግባር መግባቱንም አንስተዋል።

ከ2011 ዓ.ም ጀምሮ ተቋሙ አዳዲስ አሰራሮችንና ሪፎርም በመተግበር ላይ መሆኑን የገለጹት ዋና ሥራ አስፈጻሚው፤ በዚህም በድርጅቱ ለውጦች እየተመዘገቡ መጥተዋል ብለዋል።

በድርጅቱ በአሁኑ ወቅት የሕትመት ውጤቶች ይዘትና ተነባቢነት እንዲሁም የሰው ሀብትና የተቋሙ የመፈጸም አቅም አድጓል፣ ድርጅቱ ለተቋማት ሥልጠና ማዕከል ማዘጋጀቱና ሥጠናዎች መስጠቱ እንዲሁም የተቋሙን ገቢ ለማሳደግ አዳዲስ የገበያ አማራጮችን መጨመሩ በገቢ ደረጃ እድገት እንዲያስመዘግብ እያደረገው ስለመሆኑ አንስተዋል። በቀጣይ ማተሚያ ቤት ማቋቋም፣ የኦንላይን ቴሌቭዥን ለመጀመር የስቱዲዮ ግንባታ ማጠናቀቅና የተቋሙን የቀደሙ የካሜራና ድምጽ ሌሎች ታካዊ ሰነዶች መረጃዎች ለእይታ የሚቀርቡበት ሙዚየም ማገባደድ ይገኝበታል ብለዋል።

በሌላ በኩል የሕትመት ዋጋ በየጊዜው መናር፣ ድርጅቱ የራሱን ማተሚያ ቤት ለማቋቋም የያዘው እቅድ መዘግየት እንዲሁም ከድርጅቱ የስራ እንቅስቃሴ ጋር ተያይዞ መጠነኛ የአዋጅ ማሻሻያ የሚፈልጉ ጉዳዮች አለመሻሻላቸው እንደማነቆ አንስተው ቋሚ ኮሚቴው በእነዚህ ጉዳዮች ላይ ድጋፍ እንዲያደርግ ጠይቀዋል።

የሕግ፣ ፍትህና ዴሞክራሲ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ አባላትም ሪፖርቱን ካዳመጡ በኋላ በጥንካሬና መሻሻል ባለባቸው ጉዳዮች ዙሪያ አስተያየት ሰጥተዋል። አባላቱ ድርጅቱ የጀመራቸው ሀገራዊ አንድነትን የሚያጠናክሩ አዳዲስ አሰራሮች መጠናከር እንዳለባቸው ጠቁመው፤ በቀጣይ የድርጅቱ የሕትመት ውጤቶች ተደራሽነትን ማሳደግ፣ በሥራዎቹ የሕዝብ ድምጽ ሆኖ መቀጠል እንዲሁም የጀመረውን ተፅዕኖ ፈጣሪነት አጠናክሮ እንዲቀጥል አሳስበዋል።

የሕግ ፍትህና ዴሞክራሲ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢ ው/ሮ እጸገነት መንግስቴ የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት የጀመረው ስለ ኢትዮጵያ መድረክ ያልተለመደና አዲስ እይታ ከመሆኑም በላይ ሀገራዊ ፋይዳውም ላቅ ያለ በመሆኑም አድንቀዋል። የውይይት መድረኩ የተለያዩ ሃሳቦች እንዲንሸራሸሩ በማድረግ ሀገራዊ መግባባት ለመፍጠር የሚደረገውን ጥረት የሚያግዝም ነው ብለዋል።

በይዘት ተፅዕኖ ፈጣሪነትና አጀንዳ መሪነት፣ የሰው ሃይል አቅምን ለመገንባት እየሰራ ያለው ተግባር፣ ሀብት ለማሰባሰብ የጀመረው ጥረት እንዲሁም በዘርፈ ብዙ ተግባራት ላይ ተቋሙ የሰራቸው ሥራዎች በጠንካራ ጎን የሚጠቀሱ መሆኑንም አንስተዋል።

አክለውም በለውጥ ሂደት ውስጥ ያለው የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እያከናወናቸው ያሉ የሪፎርም ተግባራት ሊደርስበት ካቀደው ግብ የሚያደርሱና በትክክለኛ መንገድ መጓዙን የሚያረጋግጡ ናቸው፤ የሕዝብ ችግርን ለመፍታትና ሀገራዊ ተልዕኮውን ለመወጣት እያደረገ ያለው ጥረትም አበረታች ነው ብለዋል።

በቀጣይም ድርጅቱ የጀመረውን የሪፎርም ሥራ አጠናክሮ በመቀጠል፣ የበለጠ ወደ ሕዝብ ወርዶ ችግሮችን የማሳየትና የሕዝብን ድምጽ እንዲሰማ የማድረግ ብሎም የሕዝብ ተጠቃሚነትን ለማረጋገጥ መሥራት ይገባዋል ብለዋል። ከዚህም በተጨማሪ የጋዜጣ ስርጭትን በማሳደግና የመልካም አስተዳደር ችግሮችን በማጋለጥ ረገድ የጀመረውን በጎ ተግባር አጠናክሮ ሊቀጥልና ጉዳይና ብዝሃነትን ታሳቢ ያደረገ የተደራሽነት ሥራ ሊሰራ እንደሚገባውም አሳስበዋል።

# «ኢትዮጵያ...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

የአሜሪካ እና አውሮፓ ጉዳዮች ዳይሬክቶሬት ጀኔራል አምባሳደር እሸቴ ጥላሁን ገለጹ።

አምባሳደር እሸቴ ከእለት እለት እየበረታ የመጣውን የአንዳንድ የውጭ ሃይሎች ጫናን አስመልክተው ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ ማእከላዊ መንግሥት ሁል ጊዜ መሳሪያ ታጥቆ የሕዝብን ሰላምና ደህንነትን የማስከበር ሃላፊነትም፣ ሥልጣንም አለው፤ ይህ ደግሞ በመርህ ደረጃም ተቀባይነት አለው ሲሉ ገልጸዋል።

አሸባሪው ሕወሓት በሃሰተኛ ፕሮፖጋንዳ ዘመቻ የዓለምን አመለካከት ለማሳሳት ጥረት እያደረገ መሆኑን በማስታወስም፤ አሁን ያለው ትንሽ የመወናበድ ጊዜና መንፈስ ሃላፊ ነው። እውነታውን በተረዱ ጊዜ የአገራቱ ወዳጅነትና ትብብር ድሮ ወደ ነበረበት መሰረት ይመለሳል ብለን እንጠብቃለን፣ ለዛም እንሰራለን ብለዋል።

በተደጋጋሚ እያየን እንደመጣነው በእነርሱ በኩል የሚያቀነቅኑት አስተሳሰብ አለ፣ በኢትዮጵያ በኩል ደግሞ ራስን የመከላከል ትግሉ ቀጥሏል። በአሸባሪው ሕወሓት በኩል የፕሮፖጋንዳ ዘመቻ ይካሄዳል፣ ደጋፊዎቹንና ተከፋይ ጸሃፊዎችን እያንቀሳቀሰ የዓለምን አመለካከት ወደሚፈልገው አቅጣጫ የማምራት ጥረት ያደርጋል። አንዳንዶች በዚህ አስተሳሰብ ከመጠን በላይ የተገፉና የተወሰዱ ይመስላል ብለዋል።

በዚህ መልክ የሚያራምዱት አቋም አሸባሪውን ሕወሓት በሰላም ውይይቱ ወቅት የልብ ልብ ተሰምቶት የማይሆን ቅድመ ሁኔታ በማቅረብና ሰንካላ ቅድመ ሁኔታዎችን በመደርደር ለአገር ዘላቂ ሰላም ለማምጣት የሚደረገውን ጥረት እንዳያደናቅፍ የዲፕሎማሲ ጥረቱ ጥንቃቄ በተሞላበት መንገድ እንደሚቀጥልም አምባሳደር እሸቴ አመልክተዋል።

በኒውዮርክ የአሜሪካ አምባሳደር ቋሚ መልእክተኛ የሁኑት ግለሰብ በትዊታቸው ላይ ያሰፈሩት ሕወሓትና ፌዴራል መንግሥት ሁለቱም መሳሪያቸውን ያውርዱ የሚለው ሃሳብ በዓለም አቀፍ መርህ ውስጥ የሌለና ሊነገርም የማይገባ እንደሆነም ተናግረዋል።

«ማእከላዊ መንግሥት ሁል ጊዜ መሳሪያ ታጥቆ ሰላምና ደህንነትን የማስከበር ሃላፊነትም፣ ሥልጣንም አለው፣ ይህ ደግሞ በመርህም ተቀባይነት አለው» ያሉት አምባሳደር እሸቴ፤ ከአንድ ተዋጊ፣ ሽማቂ ወይም አማጺ ቡድን ጋር እኩል አድርጎ ተመሳሳይ መልእክት ማስተላለፍ ተገቢነት እንደሌለም ነው የገለጹት።

ምዕራባውያን እሴታቸው አድርገው የሚያወሯቸው፣ ነገር ግን ካለፖለቲካቸው ፍላጎት በስተቀር ተግባራዊ የማያደርጉት ነገር መኖሩን አመልክተዋል።

እንደርሳቸው ገለጻ፤ በግጭት ወይንም በጦርነት ጊዜ ሲቪሎችን ከአደጋ መጠበቅ፣ የሰብዓዊ መብት ተጠያቂነትን ማረጋገጥና መሰል ጉዳዮችን ይዘው በማናቸውም ሁኔታ ከመናገር ወደ ኋላ አይሉም።

የአሁኑን ለየት የሚያደርገው በየዕለቱ በርካታ ባለሥልጣናት አጀንዳ እያደረጉት የሚያቀነቅኑት መሆኑ ነው። ይሄ በተለያየ መልክ ሊታይ ይችላል። በአንድ በኩል በአፍሪካ ቀንድ አካባቢ ባላቸው የጂኦ እስትራቴጂክ ፍላጎት ኢትዮጵያን በሚፈልጉት አቅጣጫ ብቻ እንድትጓዝ ተጽእኖ ያደርጋሉ።

ከሰሃራ በታች ባሉ የአፍሪካ እና የመላው አፍሪካ አገራት ያወጧቸውን የእስትራቴጂ ሰነዶችን በመመልከት የዚህ አይነቱ አካሄድና ተጽእኖ የማሳደር ፍላጎት ቀጣይነት ያለው መሆኑን መገንዘብ ይቻላል። ነገር ግን ተገቢነት የለውም ብለዋል።

# «የምርት ስወራ...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

ካልቀረበ የምርት ስወራና የዋጋ ግሽበት እንዲጨምር ያደርጋል ብለዋል።

አቶ ክቡር ገና፣ በምርት አቅርቦትና ግብይት ላይ የሚስተዋለው ችግር በተለይ አከፋፋዮቹ ዘንድ ግልጽ አሰራር መዘርጋት ያስፈልጋል ያሉት አቶ ክቡር ገና፤ በመጀመሪያ አከፋፋዮቹ በምን መለኪያ እንደ ተመረጡ፤ ሲቀጥል ደግሞ በየቀኑ የሚቀርበውን ምርት በተቀናጀ መንገድ መረጃ መለዋወጥና ቁጥጥር በማድረግ መመራት አለበት ብለዋል።

ከሀገር ውስጥም ይሁን ከውጭም የሚመጡ የምግብና የቤት ውስጥ ፍጆታ ዕቃዎች አስመጪውም ሆነ አከፋፋዩ የታወቀ ነው? ምን ያክል መጠን ያለው ምርት አቅርበዋል የሚለውን በትክክል በመቆጣጠር ማን ምንም ሳያጎድል ለገበያ እንዳቀረበና ማን በምን ያክል መጠን እንደሰወረ በመለየት ተጠያቂነትን ማስፈን እነደሚገባ አስገንዝበዋል።

አቶ ክቡር ገና እንዳስታወቁት፤ ቁጥጥር ሲባል ደግሞ አምራቹ ምን ያክል እየቀረበ ነው፤ ማነው ተረክቦ ለአከፋፋዮች የሚያደርሰው ምን ያክል መጠንስ እያንዳንዱ አከፋፋይ አቅርቧል የሚለውን በዝርዝር ክትትል ማድረግ ያስፈልጋል።

ከቁጥጥሩ ባለፈ በዋናነት የማክሮ ኢኮኖሚውን ቅኝት መለየትና ምርትን መጨመር እንደሚገባ ገልጸው፤ ለምርት ስወራ ምክንያት የሚሆነው ምርት ሲያንስ መሆኑንም አስረድተዋል።

እንደ ክቡር ገና ከሆነ፤ ከዚህ ባለፈ ያለውንም ምርት በአሻጥርና ስወራ የምርት አቅርቦት እጥረትን የሚፈጥሩ አካላት ስላሉ፤ ጠበቅ ያለ ቁጥጥሩን ማድረግ ከተቻለ ችግሩን መቀነስ ይቻላል።

የምርት ስወራ የኢኮኖሚ ሁኔታውን ከሚያዛቡ ችግሮች መካከል አንዱና ምናልባትም ዋነኛ መሆኑን የጠቆሙት አቶ ክቡር ገና፤ ለአብነት ሰሞኑን የሲሚንቶ ምርትን በመደበቅ ከቀናት በኋላ ለገበያ በማቅረብ ተጨማሪ ጥቅም የማግኘት የሚጥሩ ግለሰቦች መኖራቸውን ጠቁመዋል።

ምርትን በመደበቅ ለጊዜው ትርፍ ማግኘት ቢቻልም ከምርት ስወራ ጋር ተያይዞ የሚመጣው መዘዝ ይቅር ትርፉ ዋናውን ሊያሳጣ የሚችል አደጋ መሆኑን በመገንዘብ ሁሉም በሕጋዊ መንገድ መስራት እንደሚጠበቅበት መክረዋል።

በመሆኑም ህብረተሰቡን ስለኢኮኖሚው ማስተማር ያስፈልጋል። አገር በአንድነት ሲገነባ ነው ሰላም የሚመጣው፤ አንዱ ብቻውን ምርት እየደበቀና ጠፋ ሲባል አውጥቶ እየሸጠ ትርፍ ስላካበተ ብቻውን ሊያድግ እንደማይችል ጥልቅ ግንዛቤ መስጠት ይገባል ብለዋል።

ግንዛቤው አንድም ምርት አከፋፋዩ በህጋዊነት እንዲሰራ በሌላ በኩል ህብረተሰቡም ችግር ሲያጋጥም አስገፈላጊውን መረጃ እንዲያቀብል የሚረዳ መሆኑን ገልጸው፤ ቁጥጥሩ የሕዝብ ከሆነ መንም ምንም ቢደብቅ ሊያመልጥ እንደማይችል አስረድተዋል።

# ርዕሰ አንቀፅ

## የጣልቃ ገብነትን የፖለቲካ ፍላጎቶች የሚዘጋው - ስኬታማው የስንዴ ልማት ጉዞ!

እችላለሁ ሲባል፣ መቻልን ከቃል በዘለለ ተግባር መግለጥን የሚጠይቅ ነው፡፡ ምክንያቱም ቃል በተግባር ካልታገዘ ከባዶ ዲስኩርነት አይሻገርምና ነው፡፡ በዚህ ረገድ ኢትዮጵያ እንደ አገር፤ ኢትዮጵያውያንም እንደ ሕዝብ ይቻላልን ሲናገሩ፤ እንዲሁ ለማለት ሳይሆን አድርጎ እንደሚቻል በማሳየት ጭምርም ነው፡፡ ይሄንን እውነትም፤ ነጻ አገር ሆኖ መኖር ይቻላል ብለው፤ በነጻነት ኖረው አሳይተዋል፡፡

የቅኝ ገዢን ህልም ቅዥት ማድረግ ይቻላል ብለው ተናግረው፤ ቅኝ አገዛዝን በዓድዋ ተራሮች አይቀጡ ቅጣት ቀጥተው ለሌሎች ጭቁኖችም አርዓያ ሆነው ለድል አነሳስተዋል፡፡ የአገርን ሉዓላዊነት በማንኛውም መልኩ ከሚደፍሩ የውጭም ሆነ የውስጥ ጠላቶች ራስን ተከላክሎ በክብር መኖር ይቻላል ብለው፤ ይሄንኑ በተግባር እያረጋገጡ ዛሬ ላይ አድርሰውናል፡፡

ይሄ የኢትዮጵያውያን የይቻላል ቃል እና መንፈስ በተግባር እየታገዘ በዘመን ጅረት ውስጥ ሲራመድ፤ ወታደሩ በጦር ግንባር፣ አትሌቱ በውድድር መስመር፣ አርሶአደሩ በእርሻ ማሳው ሁሉም እንደየተሰማራበት መስክ የራሱን የቤት ስራ ወስዶ ድልን ማስመዝገብ፤ ተገዳዳሪን አንገት ማስደፋት፤ ሊጫነው የሚሰነዘርበትን ክንድ እንደ አጋዥ ኃይል ወስዶ የበለጠ ወደ ድል በመገስገስ ኢትዮጵያን ዛሬም የድል እና የነጻነት ምድር አድርጓት ዘልቋል፡፡ ይሁን እንጂ በአንድም በሌላም መልኩ፤ ኢትዮጵያ በሰው ሰራሽም ሆነ በተፈጥሮ ሁነቶች ምክንያት የዳቦ ጥያቄዋን በሚፈለገው መጠን መመለስ ሳትችል፣ በተለይ ድርቅና ሌላም አደጋ በተከሰተ ቁጥር እጇን ለእርዳታ ለመዘርጋት ተገድዳ ትታያለች፡፡

ይህ ሁነት ደግሞ የይቻላል ጉዞዋን የበዙ ስኬቶች ለማጨለምና በሌላው ዘርፍ ሊጫኗት ላልቻሉ ኃይሎች እንደ ትልቅ የመግቢያ በር እድል አድርገው እንዲመለከቱት አድርጓቸዋል፡፡ ለዚህም ነው ኢትዮጵያ በችግሯ ጊዜ የሰብዓዊነት ጥያቄ ባቀረበች ቁጥር የስንዴ ጥያቄዋን ምላሽ ከፍ ካለ ፖለቲካዊ ፍላጎታቸው ማስፈጸሚያ አጀንዳዎች ጋር አያይዘው ለመመለስ ሲታትሩ የሚስተዋሉት፡፡

በዚህም ኢትዮጵያ ለበዛ ፈተናና ችግር ስትጋለጥ ኖራለች፡፡ ይሄው መዘዝ ዛሬም ድረስ እንደ አሸባሪው ትህነግ ባሉ ሆድ አደር ባንዳዎች በታገዘው እኩይ ተልእኳቸው ሊፈታተናት ሲሞክር ታይቷል፡፡

ሆኖም ኢትዮጵያውያን መርሃቸው እንችላለን፤ ፈተናዎችን በጽናት ተሻግረን ነጻነትና ክብራችንን አስጠብቀን እንራመዳለን፤ የኢትዮጵያን የመቻል ልዕልና ከፍ አድርገን እንገልጣለን፤... የሚለውን ጽኑ እምነትና አቋም በሙላት ለማራመድ የሚያስችላቸው ሁሉን አቀፍ ትግል ውስጥ ገብተዋል፡፡ ከእነዚህ የትግል አውዶች መካከል ደግሞ አንዱና ትልቁ የኢትዮጵያን በልቶ የማደር የዳቦ ጥያቄ ከመመለስ ባሻገር፣ ጉዞው የኢኮኖሚ ብልጽግናዋን ማረጋገጥ ነው፡፡

በዚህ ረገድ በተለይ በግብርናው ዘርፍ እየተከናወነ ያለው ስራ ሕያው ማሳያ ሲሆን፤ በሰብል (እንደ ስንዴና ሩዝ)፣ በአትክልት፣ በፍራፍሬ፣ ጥራጥሬና ጥጥን ጨምሮ በሌሎችም የግብርና ዘርፎች ላይ እየታየ ያለው እምርታ የኢትዮጵያውያንን የመቻል አቅም አፍ አውጥተው የሚናገሩና ሉዓላዊነትን የሚያረጋግጡ ዘመቻ እማኞች ሆነው ተገልጠዋል፡፡

በተለይ በስንዴ ልማት ዘርፉ እየታየ ያለው ከፍ ያለ ስኬት፤ ኢትዮጵያን እና የኢትዮጵያን ወዳጆች በእጅጉ ያስደሰተ፤ የኢትዮጵያን ጠላቶች ክፉኛ የስደነገጠና ያበሳጨ ተግባር ሆኗል፡፡ ምክንያቱም የስንዴ ልማቱ ስኬታማ ጉዞ የኢትዮጵያውያንን በልቶ የማደር የዳቦ ጥያቄን ከመመለስ ከፍ ያለ፣ እንደ አገር እርዳታን ተከትሎ የሚገባን የፖለቲካ ፍላጎት ሽክም የሚያራግፍ የሉዓላዊነት ጥያቄን የሚመልስ በመሆኑ ነው፡፡ የስንዴ ልማቱ ስኬታማ ጉዞ፣ የኢትዮጵያ ታሪካዊ ጠላቶች ከውስጥም ከውጭም ኃይሎች ጋር ተዳምረው ኢትዮጵያን ለማዳከም፣ ኢትዮጵያውያንን አንገት ለማስደፋት የሚችሉበትን ክንድ የሚያዳክም ታላቅ አቅም ለኢትዮጵያ የሚያጎናጽፍ ነው፡፡

ምክንያቱም የስንዴ ልማት ስኬታማ ጉዞው፣ የኢትዮጵያውያንን የእንችላለን የትናትን እውነት ዛሬም ሕያው ሆኖ ስለመቀጠሉ ማረጋገጫ የሆነ፤ በድህነታቸው በር ከእርዳታ ስንዴ ጋር ተጭኖ የሚገባ የውጭ ኃይሎች የፖለቲካ ፍላጎት አጀንዳን የሚዘጋ፤ ኢትዮጵያን ለማዳከም፣ ኢትዮጵያውያንንም አንገት ለማስደፋት ሲሉ ሰብዓዊ ድጋፍን እንደ መግቢያ በር አድርገው እየተጠቀሙ ያሉ ኃይሎች ቆም ብለው አካሄዳቸውን እንዲፈትሹ የሚያደርግ፤ ኢትዮጵያውያንም ዳግም ለአፍሪካውያንና ሌሎችም በዳቦ ጥያቄያቸው ምክንያት የውጭ ጫና ለበረታባቸው ወንድም ሕዝቦች ነጻ የመውጣት የመቻል ልዕልናን ማስተማሪያ በመሆኑ ነው፡፡

እንደ አጠቃላይ አገራዊ የስንዴ ልማት ስኬታማ ጉዞው፣ ክረምት ከበጋ ማምረትን፣ በምግብ ራስን መቻልን፣ የስንዴን ምርታማነት ማሳደግን፣ ሰፋፊ የሜካናይዜሽን እርሻዎችን ማካሄድ ለኢትዮጵያ የተነፈገ እንዳልሆነ ማሳየትን፣ የውጭ ዳረጎት ከመጠበቅ በመውጣት ወደ ውጪ ስንዴ መላክን ያረጋገጠ፤ ኢትዮጵያ ስንዴ አዘል የውጭ የፖለቲካ ፍላጎቶችን ተጽዕኖ መሻገር የምትችልበትን አቅም የሚፈጥር፤ ሌሎችም አፍሪካውያን ወንድም እህቶች እንደ ቀድሞው የኢትጵያን የመቻል አርአያነት እንዲከተሉ መንገድ የከፈተ ታላቅ ተግባር ነው!


ኢንድ

# አዲስ ዘመን

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስኪያጅ**

ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22

**ዋና አዘጋጅ**

አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**

ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ

ወረዳ 06

የቤት ቁጥር 319

ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et

ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**

ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ

ስልክ፡- 011 126 4240

Email:- wendweson.shimelis@press.et

wendwesonshimelis@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**

- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- አልማዝ አያሌው
- እስማኤል አረቦ

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**

ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com

ስልክ - 011-126-43-41

ፋክስ - 011-811-13-15

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**

ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73

ፋክስ - 011-126-58-12

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**

011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ**

ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


**ነፃ ሃሳብ**

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው፡፡ በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም፡፡

# የራሳችንን ጉዳይ ለራሳችን ተውልን !!

**ግርማ መንግሥቴ**

ጉዳዩ አዲስ መሳይ እየሆነ እንጂ የምሩን አዲስ ሆኖ አይደለም። እንደው ለደንቡ ያህል እናንሳው እንጂ ችግሩ መቼም የማይፀዳ፤ ታጥቦ ጭቃ ነገር ነው። ሁሌ ወደ ኋላ፤ ተራመደ ሲሉት እንደ በሬ ሽንት የኋልዮሽ ይንገዳገዳል። "ምኑ?" ለምትሉ፣ የምዕራባዊያኑ ተግባርና ደባ።

እንደሚታወቀው አሁን አሸባሪው ትህነግ የለም። አለ ከተባለም ያለው በአንዳንድ ወገኖች መንፈስ ውስጥ ብቻ ነው። እውነቱ ይህ ከሆነ፣ እሱ በሌለበት ስለ እሱ ህልውና የሚጨነቁ መኖራቸው ከምን የመጣ ነው ብሎ ማለት ይቻላል? ባጭሩ ማለት የሚቻለው ኢትዮጵያን የማጥቃት ግልፅ (ድሮ ድብቅ ከሆነ) አጀንዳና በዘመናዊ ቅኝ አገዛዝ ስር ለማድረግ ያለመ፤ ያፈጠጠ ቂልነት የወለደው ስግብግብነት ነው።

ይህንን ስንል ዝም ብለን አይደለም። አሜሪካ መራሹ ምእራቡ አለም ምን ያህል፣ በተቀነባበረና በተናበበ አሰራር በኢትዮጵያ ላይ እያካሄዱት ያለውን ከስም ማጥፋት የዘለለ የማጥቃት ተግባር እንዳለ ስለምናውቅ ነው። ይህንን መሬት ለማስረገጥ በዚሁ በኦክቶበር ብቻ ከተደረጉት የተወሰኑትን ብቻ እናንሳ።

በተቀነባበረና በተናበበ ... ሁኔታ፣ በአገራትና ትላልቅ ተቋማት (ከመስራቾቹ አንዷ በመሆን የመሰረተችው የተባበሩት መንግስታት ሳይቀር) ከሚሰሩት በባሰ በሚዲያው (ሚዲያው የእነሱ አንደበት መሆኑ ቢታወቅም) እየተሰራ ያለው የከፋ ነው።

በሚዲያው ከተሰሩት ፀረኢትዮጵያ እንቅስቃሴዎች መካከል The New York Times (October 9 2022), The Chicago Tribune (Oct. 2022) – በዚሁ እለት፣ ከዚሁ ጋዜጣ ጋር በተናበበ መልኩ "ሪፖርት" ያለውን የለቀቀው The Crisis Group, The Guardian (Oct. 23 2022) - ይህም ሌላው የሪፖርቱ ግልባጭ ነው፤ አሁን በዚሁ ሰሞን ደግሞ Forbs, ussanews እና ሌሎችንም መጥቀስ ይቻላል (በእነ newsnow የሚለቀቀው ሳይረሳ ማለት ነው)።

የዚህ ጽሑፍ አላማ የእነሱን ከሁሉ ነገሩ ጋር የተጣላ ትርክት እዚህ መድገም ባለመሆኑ የእነሱን በዚሁ ትተን ስለ ነበረው፣ የተካሄደው ጦርነት አንዳንድ ጉዳዮችን እናንሳ። እርግጥ ነው፣ ዛሬ እንዲህ በሰፈረው ቁና ሊሰፈር፣ ወደ ጦርነት ዘሎ የገባው አሸባሪው ትህነግ ነው። ያቅራራውም ቡድኑ ነው። በመከላከያ ላይ የለሌ ጭካኔን ተግባራዊ በማድረግ ወደ ለየለት የአገር ክህደትና ጦርነት የገባው እሱው ነው።

አገርና ህዝብንም አሳልፎ ለባእድ የሰጠውም፤ የዚህ ሁሉ ወጣት፣ ሴቶችና ህፃናት ደም ይፈስ ዘንድ ምክንያቱ ይኸው ቡድን ነው። በመከራ የተሰራ ሀብትና ንብረት ይወድም ዘንድ እሳቱን የለኮሰው እሱው ነው። ይሁን እንጂ ከላይ የጠቀስናቸውም ሆኑ መሰሎቻቸው እየካዱት ያለው የፕሮፓጋንዳ ዘመቻ ፣ በቻሉት ሁሉ ቡድኑን ነፃ ለማድረግ ነው።

"ለመሆኑ ጦርነቱ በማንና በማን መካከል ነበር?" ብለን እንጠይቅና ለእነሱ ግልፅ በሚሆን መልኩ (የሚያውቁት ቢሆንም) መልስ እንስጥ። ከዛሬ ጀምሮ ጨርሰው ይፋቱን ዘንድም እንነገራቸው።

አለመታደል ሆኖ ጦርነቱ በአንድ እናት ልጆች መካከል መካሄዱ ይታወቃል። የአንድ እናት ልጆች ይሁኑ እንጂ የተነሱበት አላማ ፍፁም ተቃራኒ ሲሆን የተቃርኖው ማእከልም ኢትዮጵያና ኢትዮጵያውያን ናቸው። ባጭሩ፣ ኢትዮጵያን የማፍረስ እኩይ ዓላማ እና ኢትዮጵያን የማዳን ዓላማ ባነገቡ ሀይሎች መካከል ነው።

ጦርነቱ የነበረው በአገር ወዳዶችና አገር ጠሎች መካከል ነው። ጦርነቱ የነበረው በሽብር ቡድኖችና ፀረሽብር ቡድን መካከል ነበር። ጦርነቱ የነበረው የህግ የበላይነት ይከበርና አይከበር በሚሉ ወገኖች መካከል ነው። ጦርነቱ የተጀመረው ስልጣን በዲሞክራሲያዊ መንገድ መሸጋገር አለበትና የለበትም በሚሉ አካላት መካከል ነው።

ጦርነቱ የማህበረሰቡን እሴቶች ድምጥማጣቸውን ካላጠፋሁ በሚሉና የለም ንክች አታደርጋትም በሚሉ ወገኖች መካከል ነው። ጦርነቱ በአገር ግንባታ ተግባር ላይ በተሰማራ አካልና በአገር ማፍረስ ተግባር ላይ በተሰማሩ አካላት መካከል ነበር። ውጊያው የከፋፍለህ ግዛው ፖለቲካን በማራመድና ባለማራመድ፤ በማስቀጠልና ባለማስቀጠል መካከል ነበር።

ጦርነቱ የሩዋንዳውን ኢንተርሀምዌይ በኢትዮጵያ መድገም በሚፈልግና የለም አታደርጋትም በሚሉ ሀይሎች መካከል እንደ ነበር አሳምረው የሚያውቁት ምእራባውያን፣ የተለመደውን "አሳስቦኛል ..."፣ "ከንክኖኛል ..." ማለትን እንኳን በመተው ጭራሽ ሁሉም ነገር ወደ ነበረበት እንዲመለስ እየፈለጉ ነው ያሉት።

ጦርነቱ ዲሞክራሲያዊ ስርአትን በመገንባትና ባለመገንባት፤ የአገር ሉአላዊነትን በማክበር፣ ማስከበርና ባለማክበርና ባለማስከበር መካለል ነበር ሲካሄድ የነበረው። በመሆኑም፣ አገርን በማዳን ተግባር ላይ የተሰማራው ሀይል አሸነፈ። ይህ ደግሞ የነበረ፣ ያለና የሚኖር እንጂ ዛሬ የሆነ፣ ድንገት መጥቶ አይደለም። ከላይ የጠቀስናቸው የምእራቡ ዓለም ሚዲያዎችም ሆኑ እነ ብሊንከን፣ ሳማንታ ፓወርና ቡድናቸው፣ የአውሮፓ ህብረት፣ ዩኤን ... ያልተገነዘቡት ይህንን ነው።

ጦርነቱ ደካማ መንግስት በመፍጠርና ጠንካራ ስርአትን በማስቀጠል መካከል የነበረ መሆኑን ጠንቅቀው የሚያውቁት የምእራቡ ዓለም ሚዲያና ባለ ስልጣናት ልክ እንዳላወቁ ሁሉ፣ ዛሬም፣ ለሌለው አሸባሪው ሕወሓት ወገባቸውን አስረው ለሌላ እስትንፋሱ ይፀልያሉ፤ ለተዝለፈለፈ ጉልበቱ መቅኔ ለመሆን ይታትራሉ።

"የአገር መከላከያ ሠራዊት ዋንኛ ተልዕኮ የሽብር ቡድኑን ወታደራዊ አቅም ማዳከምና ቡድኑ ሰብዓዊ ጋሻ ያደረጋቸውን ንጹሓን ዜጎች ነጻ ማውጣት ነው" የሚለውን የመከላከያ መግለጫ እንኳን መስማት አይፈልጉም። ይህ መግለጫ እነሱ ጋ ሲደርስ ዘር ማጥፋት ሆኖ ቁጭ ይላል። እራሳቸው ያስገቧቸውን ከ5 ሺህ በላይ ትራኮች ረስተው (ቡድኑ ለጦርነት ማዋሉ አንድ ጉዳይ ሆኖ) እርዳታ ማድረስ እንኳን አልተቻለም በማለት መክሰስን ስራዬ ብለው ተያይዘውታል።

የመከላከያ መግለጫም የሚነግረን ይህንኑ ሲሆን፤ ጉዳዩንም እንደሚከተለው ነበር ያስቀመጠው፤ "ሽብር ቡድኑ ንጹሓን ዜጎች ጉዳት ደርሶባቸዋል በሚል በርካታ ያቀናበራቸው ሐሰተኛ ተንቀሳቃሽ ምስሎች በማስረጃነት መገኘታቸው ይፋ መደረጉን ሊቀበሉ አልፈለጉም። አሸባሪው ትህነግ ንጹሓን ዜጎችን አደጋ ላይ በመጣል ሐሰተኛ ተጎጂዎችን በመፈብረክ በርካታ ያቀናበራቸው ሐሰተኛ ተንቀሳቃሽ ምስሎች በማስረጃነት መገኘታቸውን" እያዩ አለማየትን፤ እየሰሙ አለመስማትን የመረጡ ሲሆን፣ የተሻለ ሆኖ ያገኙት ግን አሁንም ኢትዮጵያን ማፍረስ ላይ መጠመድን ነው።

ይህ ሁሉ አይቶ እንዳላየ ሰምቶ እንዳልሰማ፤ መግለጫው ብዙ ቢሆንም፤ እኛ ግን ለራሳችን ጉዳይ በቂና ከበቂ በላይ ስለሆንን የራሳችንን ጉዳይ ለራሳችን ተውልን ! ተውን !!! (Leave US alone!!!)

# ነፃ ሃሳብ

## አገራችንን ለመታደግ እስከየት ድረስ ተጉዘናል፤ ለመጓዝስ ወስነናል ?

**በትረ ሙሴ (መልክ ኢትዮጵ)**

አገራችን ኢትዮጵያ በዓለም አቀፍ ጦርነት ውስጥ ናት። ከአሸባሪው ሕወሓት ጋር ብቻ ሳይሆን የቡድኑ ወዳጅና ደጋፊ ከሆኑ አገራት ጋር ጭምር ግልጽ የሆነ ጦርነት ውስጥ ነች። ይሄን እውነት ለማወቅ ጠቢብ መሆን አይጠበቅብንም። የምናየው የምንሰማው ሁሉ አገራችን በዓለም አቀፍ ጦርነት ውስጥ እንዳለች የሚመሰክር ነው። በዚህም ላለፉት ሁለት ዓመታት ከፍ ባለ የአገር ውስጥና የውጪ ጫናዎች ውስጥ ነበረች።

በጫናዎች ውስጥ እንደአገር ብዙ ዋጋ ከፍለናል። በህልውናው ለመጣበት ድርድር የማያውቀው የኢትዮጵያ ህዝብ በአንድነት በመወገን በብዙ ጫና ሰልፍ የወጡበትን ጠላቶቹን አሳፍሯል። ዛሬ ላይም ቢሆን በተመሳሳይ መንገድ እለ አገሩ ዘብ በመቆም የጠላቶቹን ሕልም እያከሸፈ ይገኛል።

ከአገር ውስጥ አሸባራው ሕወሓትና ሸኔ ከሌሎች ታጣቂ ኃይሎች ጋር በመሆን፣ ከውጪ ደግሞ ታሪካዊ ጠላቶቻችንንና ከአካባቢው ያልተገባ ጥቅም የሚፈልጉ ኃይሎች በመናበብ በጫና ሊያንበረክኩን ረጅም ርቀት ሄደዋል። ግልጽ ጦርነት አውጀው በአደባባይ ተገዳድረውናል።

በዓለም አቀፍ የመገናኛ ብዙሀን የተቀናጀ የፕሮፓጋንዳ ዘመቻችን ከማካሄድ ጀምሮ እስከ ማእቀብ የደረሱ ማእቀቦችን ጥለውብናል። በተቀጣሪ አክቲቪስቶችን የበሬ ወለድ ዘገባዎች አገራዊ እውነታችን በማጠልሸት ዓለም ስለ ኢትዮጵያ ትክክለኛውን ነገር እንዳይረዳ በትጋት ሰርተዋል። ሁሉም ግን እንዳሰቡት አልሆነላቸውም። በዚህ ሁሉ ዘመቻ ለኢትዮጵያ የሚያስቡ፣ እውነታችንን ተረድተው ከጎናችን የቆሙ አገራት የሉም ማለት አይደለም፤ ነበሩ ።

ሕወሓት እንደ ነፃ አውጪ ድርጅት በደደቢት በርሀ በሰይጣናዊ ሀሳብ የተወለደ ነው። ይህ ቡድን ለአገርና ህዝብ መልካም ነገር ይሰራል ብሎ ማሰብ የዋህነት ነው። ዛሬም ድረስ ኢትዮጵያና ህዝቦቿ እየተሰቃየንበት ያለው በዚህ ቡድን ሀሳብና የፖለቲካ ፍልስፍና ነው።

ቡድኑ ገና ከውልደቱ ጀምሮ ብቻውን ሆና አያውቅም። ከጽንሰቱ ጀምሮ እስከ ውልደቱ ድረስ በብዙ ፀረ-ኢትዮጵያዊ ሀይሎች ሲደገፍ የኖረና አሁንም እየተደገፈ ያለ ሀይል ነው። አቅም ትምክህቶቹም እነዚህ ሀይሎች ናቸው። ከነዚህ ሀይሎች ውጪ ህይወት የለውም። ዛሬ ላይም ተፈጥሯዊ ሞቱን ከመሞት ይልቅ በነዚህ ሀይሎች ህይወቱን ለመዝራት የሚያደርገው ጥረት የዚህ እውነታ ተጨባጭ ማሳያ ነው።

ከትጥቅ ትግል ወደ ስልጣን የመጣው በነዚህ ሀይሎች ትከሻ ላይ ታዝሎ ነው። ለ ሀያ ሰባት አመታት ስልጣን ላይ የቆየውም በነዚህ ሀይሎች ድጋፍ ነበር። ከስልጣን ከተባረረች ማግስትም ወደ ስልጣን በሀይል ለመመለስ የሄደበት የጥፋት መንገድ በነሱው ታምኖ ነው።

ያለፉት ሁለት የጦርነት አመታት በስተጀርባ የእነዚህ ሀይሎች ፍላጎት ለማስፈጸም በአሸባሪው/ባንዳ ሕውሓት በኩል የተካሄደ ነው። አላማውም በራሷ የምትተማመንና ለሌሎች ጥቁር አፍሪካውያን ወንድሞቻችን ምሳሌ የምትሆን አገር ተፈጥራ ላለማየት ነው። ለዚህም ሀገሪቱን ባልተገባ መንገድ ዓለም አቀፍ አጀንዳ ለማድረግ የተሄደበት ርቀት ማሳያ ነው።

አገሪቱ ባለፉት ሁለት አመታት ታይቶና ተሰምቶ በማያቅ ሁኔታ በተባበሩት መንግስታት ድርጅት የጸጥታው ምክር ቤት በኩል ዓለም አቀፍ አጀንዳ ለማድረግ ተሞክረዋል አብዛኞቹ ስብሰባዎች ለአሸባሪው ሕወሓት አጋርነትን የመግለጽ ያህል እስኪመስሉ ድረስ ትዝብትን ፈጥረው አልፈዋል።

አሸባሪው ሕወሓት በኢትዮጵያ ምድር ሁሉንም አይነት ግፍ ፈጽሟል። የትም መቼም በማንም ላይ ያልደረሱ ሰብዐዊ ግፎችን በገዛ አገሩና ወገኑ ላይ አድርሷል። ዓለም አቀፉን የጦርነት ህግ በጣሰ መልኩ ሁሉንም አይነት ግፍ ሰርቷል። በዚህ ሁሉ ውስጥ ግን ቡድኑ በአደባባይ በትምክህት ለፈፀማቸው ግፎች የጠየቀው ሆነ ለህግ ይቅረብ ያለው አካል የለም። ከዚህ ይልቅ ዓለም አቀፍ ተቋማትን ጨምሮ ለሰብአዊ መብቶች ተሟጋች ነን የሚሉ አገራት ሳይቀር ዝምታን እና አይቶ አለማየትን መርጠዋል።

አሸባሪው ሕወሓት ለስልጣን ጥማቱ ሲል በየትኛውም ሀይል ከመጋለብ ወደ ኋላ የሚል አይደለም። ከውልደቱ ጀምሮ ያለው ታሪኩ በዚህ ባህሪው የተሞላ ነው። ከታሪካዊ ጠላቶቻችን አንስቶ በየወቅቱ በአገራችን፣ በህዝባችን ጥቅምና ፍላጎት ላይ ለተነሱ ጠላቶቻችን ዋነኛ መሳሪያ ሆኖ አገልግሏል። በዚህም አገርን እስከ ማፍረስ የደረሰ የባንዳነት ተልእኮ ፈጽሟል።

የለውጡ መንግስት ሆነ በለውጡ አስተዳደር ስር ያለው መላው ህዝባችን ለቡድኑ ማንነትና ከማንነቱ ለሚመነጨው ሴራ እንግዳ አይደለም። ከዚህ የተነሳም ቡድኑን አምርሮ እየተዋጋ ይገኛል። ቀጣይ እጣ ፈንታው አገር ከዚህ ቡድን የባንዳነት ተልእኮ ነጻ ስትሆን እንደሆነም ከትናንትና እና ከዛሬ ታሪኩ በሚገባ ተረድቷል። ለዚህ አስረጅ የሚፈልግበት የመረጃ ክፍተት የለበትም።

ኢትዮጵያውያን ለችግሮቻችው ከመቼውም ጊዜ በላይ ለችግሮቻችው መፍትሄ እንደሆኑ የተረዱበት ወቅት አሁን ነው። የችግሮቻችን ዋነኛ ባለቤት ያውቃሉ፤ መፍትሄውም ምን እንደሆነ ይረዳል። በዚህ ጉዳይ የውጪውን ዓለም እርዳታ አይፈልጉም። ከፈለጉም የመፍትሄው አካል እንዲሆኑ እንጂ የችግሩ አቅም እንዲሆኑ አይደለም።

አሸባሪውን ሕወሓት ለራሳቸው ፍላጎትና ጥቅም እየጋለቡ ያሉ ሀይሎች ቡድኑን ዳግም ወደ ስልጣን ህልማቸውን እውን ለማድረግ እየሄዱበት ያለው የሴራ መንገድ እንደ አገር ሊያስከፍለን የሚችለው ዋጋ ብዙ ሊሆን ይችላል እንጂ ከተነሳንለት የለውጥ አላማና ግብ የሚያደናቅፈን አይደለም።

በዚህ ሁሉ ዓለም አቀፍ ጦርነት እና ጫና እንደ አገር እስከ ሙሉ ክብሯ የመቆየቷ ነገር የዚህ ተጨባጭ እውነታ ማሳያ ነው። ይህ ጦርነት እና ጫና በሌላ አፍሪካዊ አገር ሆኖ ቢሆን ኖሮ ምን ሊከሰት እንደሚችል መገመት አያቅትም። በተመሳሳይ ጦርነትና ጫና የፈራረሱ አገራትን ቀደም ሲል የነበራቸውን አገራት ቁመና ማሰብ ደግሞ ኢትዮጵያዊነት በርግጥም የጽናት ምልክት መሆኑን ማረጋገጫ ነው።

እኛ ለእውነት ስለቆምን የቆምንለት እውነት ደግፎናል። ለእውነት መቆማችን መከራዎቻችንን ችለን እንድንጸና አድርጎናል። ወደፊትም ለሚፈጠርብን የክፉዎች ሀሳብ እንደማንወድቅ ይሄ ማረጋገጫችን ነው። በአንድነት በመቆም ድል ያደረግናቸው በርካታ ታሪኮች አሉን። ዛሬም ይህንን አለም አቀፍ ጦርነት እና ጫና በአንድነት የመከትንበት ታሪካችን የማንነታችን ተጨማሪ መገለጫ ሆኖ በትውልዶች መካከል የሚታወስ ይሆናል።

> **እኛ ለእውነት ስለቆምን የቆምንለት እውነት ደግፎናል። ለእውነት መቆማችን መከራዎቻችንን ችለን እንድንጸና አድርጎናል። ወደፊትም ለሚፈጠርብን የክፉዎች ሀሳብ እንደማንወድቅ ይሄ ማረጋገጫችን ነው። በአንድነት በመቆም ድል ያደረግናቸው በርካታ ታሪኮች አሉን። ዛሬም ይህንን አለም አቀፍ ጦርነት እና ጫና በአንድነት የመከትንበት ታሪካችን የማንነታችን ተጨማሪ መገለጫ ሆኖ በትውልዶች መካከል የሚታወስ ይሆናል**

እንደ ቀደመው ትውልድ በአሁኑ ሰዐት ሀገራችንን ከግፈኞች ለመጠበቅ ከራሳችን በቀር ልንተማመንበት የሚያስችል አንዳች ነገር የለንም። መተማመኛችን አንድነታችንና የምንሞትላት አገር እንዳለችን ማሰብ ብቻ ነው። መተማመኛችን የህዝባችን የአገር ፍቅር ስሜትና የአትንኩኝ ባይነት የታሪክ ገድል ነው። መተማመኛችን ኢትዮጵያን የሚሉ ልቦች ናቸው። መተማመኛችን አገሬን ለባዕድ አሳልፌ አልሰጥም የሚሉ መልካም ሀሳቦች ናቸው። መተማመኛችን በአባቶቻችን መንፈስ በወንድማማችነት መቆማችን ነው። እንደ አገርም ሆነ እንደ መንግስት መተማመኛችን ይሄ ብቻ ነው።

አሸባሪው ሕወሓት ለሶስተኛ ጊዜ በከፈተብን ጦርነት የመሳሪያ፣ የሎጅስቲክስና የፕሮፓጋንዳ ድጋፍ የሚሰጡ ታሪካዊ ጠላቶቻችንን ጨምሮ ሌሎች ኃይሎችን እንደጀመረው አፍ ማስያዝ/ማሳፈር የዚህ ትውልድ ትልቁ ኃላፊነት ነው፡፡ ለዚህም የታሪክና የሞራል ግዴታም አለበት።

በዚህ ዘመን እንደቀደሙት ዘመናት ለጀመርነው ለውጥ ተግዳሮት በመሆን ዓለም አቀፍ አደባባዮችን የሞሉት የአሜሪካ አስተዳደር /የባይደን አስተዳደር / እና የአውሮፓ ህብረት አባል የሆኑ አንዳንድ አገራት ናቸው። እነዚህ አገራት ለኢትዮጵያ እውነት ለመወገን አቅም የማጣታቸው እውነታ ለማንም የሚሰወር አይደል። ከቻሉ አሸባሪውን ቡድን ወደ ስልጣን ማምጣት ፍላጎታቸውን በኢትዮጵያ ህዝብ ላይ መጫን ነው።

የጦርነቱ መጀመር ሰሞን አንቶኒዮ ጉተሬዝ እንዲህ ብለው ነበር ‹ጦርነት ለሕወሓት ያደገበት ስለሆነ የኢትዮጵያ መንግስት ባይዋጋ ነው የሚሻለው› ብለው ነበር። ይሄ ንግግር በየትኛውም መመዘኛ አለም አቀፍ ተቋም ከሚመራ ግለሰብ የሚጠበቅ አልነበረም። የተነገረው ግን በአጋጣሚ አልነበረወም፤ ንግግሩ ለአሸባሪው ብድን የቱን ያህል የጥፋት ትምክህት እንደሆነው ማሰብ አይከብድም።

ከሰሞኑ ደግሞ እኚሁ ግለሰብ ‹ተደራደሩና ጠመንጃችሁን አስቀምጡ የሚለው ነገር ትልቅ ነገር አይደለም ትልቁ ቁም ነገር የኤርትራ ሰራዊት ከኢትዮጵያ ድንበር ይውጣ የሚለው ነው። ሲሉ ተደምጠዋል።

ከውጪው አለም እንዲህ አይነት መልዕክት ያላቸውን ብዙ ንግግሮች መጥቀስ ይቻላል። ሀሳብን ያነሳሁበት አሜሪካ፤ አንዳንድ የአውሮፓ አገራት ሆኑ እነሱ የሚዘውሯቸው ዓለም አቀፍ ተቋማት የቱን ያህል ኢትዮጵያን በተመለከተ እየሄዱበት ያለው መንገድ የተሳሳተና የተዛባ መሆኑን ለማሳየት ነው።

አላማቸው ከተሳካላቸው አሸባሪውን ሕወሓት በመደገፍ ወደ ስልጣን ማምጣትና እንደፈለጉ አሻንጉሊት መንግስት በመፍጠር ለዘመናት እየሄዱበት ያለውን መንገድ በኢትዮጵያ እውን ማድረግ ነው። ይህ ደግሞ ለህዝባችን ምን ማለት ሊሆን እንዲችል ነጋሪ የሚሻ አይሆንም ።

እንደ አገር ወደ ለውጥ የመጣነው ከዚህ አለም አቀፍ እውነታ እራሳችንን በመታደግ የራሳችንን እጣ ፈንታ በራሳችን ለመወሰን ነው። ለዚህ ደግሞ በቂ መነቃቃትና ዝግጅት አለን። በጫናና በማዋከብ የሚፈጠር ምንም ነገር አይኖርም። የተረከብናት አገር በብዙ መስዋእትነት የተፈጠረችና ከትውልድ ወደ ትውልድ ስትሸጋገር የኖረች ነች።

ትውልዱ የገባበት እልህ አስጨራሽ ትግል የአገርን ህልውና ለማስጠበቅና የህዝባችንን የመልማት መሻት እውን ለማድረግ ነው ። ትግሉ በልጆቿ ሀሳብ፣ እውነት እና ታሪክ አዲሲቷን ኢትዮጵያ ለመፍጠርና ለጥቁር ህዝቦች ተምሳሌት ለመሆን ነው።

ለዚህም ይህን መሰረታዊ ጥያቄ ሁሉም ዜጋ ሊጠይቅ ይገባል፤ አሸባሪው ሕወሓት በባንዳነት አገር ለማፍረስ እስከ ሲኦል ለመውረድ ከራሱ ጋር መማማሉ የአደባባይ ሚስጥር ነው፤ እኛስ አገራችንን ለመታደግ እስከየት ድረስ ተጉዘናል፤ ለመጓዝስ ወስነናል?

ኢኮኖሚ

# ሳይንስና ቴክኖሎጂ

## የሰው ሰራሽ አስተውሎት ቴክኖሎጂና በሳይንስ ሙዚየም የቀረቡ ግኝቶች

**ዳግም ከበደ**

የኢትዮጵያ አርቲፊሻል ኢንተለጀንስ ኢንስቲትዩት በቅርቡ ተመርቆ እየተጎበኘ ባለው በሳይንስ ሙዚየም ለእይታ እየቀረበ ባለው አውደ ርእይ ላይ ስራዎቻቸውን ለእይታ ካቀረቡ በርካታ የመንግስትና የግል ተሳታፊዎች መካከል አንዱ ነው። አርቲፊሻል ኢንተለጀንስ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በመንግስት ልዩ ትኩረት ተሰጥቷቸው ካሉ የቴክኖሎጂ ዘርፎች መካከል አንዱ ሲሆን፣ ኢንስቲትዩቱም ከዚህ አኳያ በርካታ ተግባሮችን እንዲያከናውን ኃላፊነት ተሰጥቶታል።

በሳይንስና ቴክኖሎጂ አውደ ርእዩ ላይ ተቋሙ እስካሁን ያከናወናቸውን ተግባራት ከፍተኛ ቁጥር ያላቸው የተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎች እየጎበኙት ሲሆን፣ ከእነዚህ መካከልም የመንግስት እና የግል ትምህርት ቤት ተማሪዎች ይገኙበታል። ተማሪዎቹ በጉብኝታቸው ስለአርቲፊሻል ኢንተለጀንስ ቴክኖሎጂ ምንነት እና ቴክኖሎጂው ጥቅም ላይ እየዋለባቸው ስለሚገኙ ዘርፎች በኢንስቲትዩቱ ባለሙያዎች ገለጻ እየተደረገላቸው ነው። በዚህም የአርቲፊሻል ኢንተለጀንስ ኢንስቲትዩት ቴክኖሎጂውን በመጠቀም በጤና፣ በቋንቋ፣ ስማርት ሲቲ፣ ሮቦቲክስ እና ተያያዥ ዘርፎች እየሰራቸው የሚገኙ የምርምር ስራዎች እንዲሁም ምርት እና አገልግሎቶችን እያስተዋወቀ ይገኛል።

ኢንስቲትዩቱ ታዳጊዎች የተለያዩ የሳይንስ እና ቴክኖሎጂ ውጤቶችን ተመልክተው ወደ ዘርፉ እንዲሳቡ በማድረግ ረገድ የሚኖረው ሚና ከፍተኛ እንደመሆኑ በሳይንስ ሙዚየም በተዘጋጀው አውደ ርእይ ላይ ኢንስቲትዩቱ የተለያዩ ሁነቶችን አዘጋጅቶ ማቅረቡን የዝግጅት ክፍላችን በስፍራው ተገኝቶ ለመመልከት ችሏል። ከእነዚህ መካከል የሰው ሰራሽ አስተውሎት ላይ መሠረት አድርገው በተቋሙ ከቀረቡ ሥርዓቶች መካከል የጡት ካንሰር ልየታ መተግበሪያ አንዱ ነው።

መተግበሪያው ሰዎች የጡት ካንሰር እንዳለባቸው ሲጠረጠር የሚታዘዘውን ማሞግራም (የጡት ኤክስ ሬይ) በቀላሉ በማንበብ የበሽታውን መኖር አለመኖር የሚጠቁም ነው። በዚህ ቴክኖሎጂ በሽታውን ቀድሞ ለመከላከል እና ለመቆጣጠር የሰውን ልጅ ዕውቀት ለማሽን ማስተማር ትኩረት ተሰጥቶታል። ይህም ተግባር በአገራችን በውስን ቁጥር የሚገኙትን የዘርፉ ባለሙያዎች በፍትሃዊነት ለዜጎች ለማዳረስ ያስችላል። የጤና ዘርፉን ለማዘመን እና ለማሻሻል ተስፋ የተጣለበት ይህ ቴክኖሎጂ፣ በቀጣይ በስፋት ምርመራ ለማድረግ እና የእናቶችን ጤና ለመጠበቅ ተጨማሪ አቅም እንደሚሆን ይታመናል።

ሌላው ተቋሙ በሙዚየሙ ያቀረበው ሁነት "አፍሪካን በአርቲፊሻል ኢንተለጀንስ ማብቃት" በሚል መሪ ቃል በመጀመሪያዎቹ ሁለት ቀናት የተካሄደው ዓውደ ጥናት ነው። አውደ ጥናቱም አርቲፊሻል ኢንተለጀንስ ቴክኖሎጂ የአህጉሪቷን መፃኢ ዕድል የተቃና በማድረግ ረገድ ስለሚኖረው ሚና ተመክሮበታል። ሀያ አምስት የሚደርሱ ጥናታዊ ጽሁፎችም በኢንስቲትዩቱ ተመራማሪዎች እና ተጋባዥ እንግዶች በዓውደ ጥናቱ ቀርበው ውይይት ተደርጎባቸዋል።

ለሳይንቲስቶች፣ ለተማሪዎች፣ ለዓለም አቀፉ ማህበረሰብ ለምርምር እና እይታ ክፍት የተደረገው የሳይንስ ሙዚየም ከተከፈተ በኋላ ባሉት 21 ቀናት ብቻ 370 ሺ የሚሆኑ የአገር ውስጥ እና የውጪ ጎብኚዎች እንደጎበኙት መረጃዎች ያመለክታሉ። በዚህ ስፍራ የምርምር ውጤቶቻቸውን እና የሳይንስና ቴክኖሎጂ የፈጠራ ውጤቶችን ካቀረቡት መካከል ከላይ ያነሳነው የአርቲፊሻል ኢንተለጀንት ኢንስቲቲዩት ይገኝበታል። በዚህም በበርካታ ሺዎች የሚቆጠር ህብረተሰብ የተቋሙን ምንነትና አጠቃላይ የምርምር ውጤቶች ለመመልከት እድሉን አግኝቷል።

በሳይንስ ሙዚዬሙ ጎብኚዎችን በማስተናገድና ገለጻ በማድረግ ላይ እንዳለች ያገኘናት ኬቲምን ተስፋዬ የኢትዮጵያ አርቲፊሻል ኢንተለጀንስ የሪሰርችና ዴቨሎፕመንት ቡድን አባል ነች። በተለይ በሮቦቶክና ኢንዱስትሪያል አውቶሜሽን ዲቪዥን ውስጥ በሚደረግ የምርምር ተግባር ውስጥ ከባልደረቦቿ ጋር በትብብር ትሰራለች። እርሷ እንደምትለው፤ ተቋሙ በሙዚዬሙ በርካታ ውጤታማ የምርምር ስራዎችን ይዞ ቀርቧል።



በሙዚየሙ የቀረቡ የሳይንስና ቴክኖሎጂ ግኝቶችን በየእለቱ እየሄዱ በስፋት እየጎበኙ ከሚገኙት የማህበረሰብ ክፍሎች መካከል በበርካታ ተማሪዎች ይገኙበታል።

ኬቲም እና የቡድን ባልደረቦቿ በዲቪዥናቸው የሮቦ ሴኪውሪቲ ቴክኖሎጂን ነው ይዘው የቀረቡት። እንደ እርሷ ገለፃ፤ ይህ ተንቀሳቃሽ ቁጥጥርና ጥበቃን የሚያደርግ ሮቦ ሴኪውሪቲ አሁን በሙከራ ደረጃ የተሰራ ሲሆን፣ ሙሉ ለሙሉ ወደ ትግበራና ምርት ሲገባ በተለያዩ መደብሮች እንዲሁም ህዝብ በሚበዛባቸው ስፍራዎች፣ ህንፃዎችና ጥበቃ በሚያስፈልግባቸው ቦታዎች ሁሉ ውጤታማ ወንጀልን የመከላከል እና ቁጥጥር የማድረግ ተግባርን ማከናወን የሚችል ነው። ከዚህ ባሻገር ምርምሩና አጠቃላይ የቴክኖሎጂ ማበልፀግ ስራው እያደገ በሚመጣበት ወቅት ደግሞ የሮቦት ወታደር ሚናን ይዞ በመከላከያ ውስጥ የሚደረግ ተልእኮን እንደሚፈፅም ገልፃልናለች።

በዚህ ዲቪዥን ውስጥ ለጎብኚዎች ከቀረቡት የሮቦት ቴክኖሎጂዎች መካከል "ሰላም" የሚል ስያሜ ያላት ደግሞ የቱሪዝም ሴክተሩ ላይ ተጨማሪ የቴክኖሎጂ እሴት እንድትሆን ዲዛይን ተደርጋ እንደተሰራች ትናገራለች። መንግስት ዘርፉን በዘመናዊ ቴክኖሎጂ በመደገፍ ለማሳደግ የሚያደርገውን ጥረት የኢትዮጵያ አርቲፊሻል ኢንተለጀንት እንደሚደግፍ የምትናገረው የዲቪዥኑ ባለሙያ በቀጣይ ግዜያትም ተመሳሳይ የምርምርና የፈጠራ ክንውኖችን ተግባራዊ እንደሚሆኑ ትናገራለች። በግብርናው፣ በህክምናውና በሌሎች ወሳኝ የሚባሉ ዘርፎች ላይ በሰው ሰራሽ አስተውሎት እና መሰል የቴክኖሎጂ ምርምር ውጤቶች ለመሸፈን እየተሰራ መሆኑን ገልፃልናለች።

"በሳይንስ ሙዚየም ውስጥ ህፃናት፣ ወጣቶችና በርካታ ሰዎች መጥተው እየጎበኙን ነው" የምትለው ኬቲም፤ ይህን መሰል እድል በመንግስት መፈጠሩ ኢትዮጵያ በቴክኖሎጂው ዘርፍ ላይ ውጤታማ ስራዎችን እንድታከናውን እንደሚያግዛት ትናገራለች። በተለይ ህፃናት መሰል የሳይንስና ቴክኖሎጂ እድገቶችን እያዩና እየተማሩ በመጡ ቁጥር ትውልዱ በእውቀትና በክህሎት የዳበረ ሆኖ እንደሚቀረፅ ትገልፃለች። ለትውልዱ መሰረት የሚሆን ስራዎችን ለመስራት አበረታች መሆኑን ትገልፃለች።

ወጣት ኤፍሬም አበበ ይባላል። በኢትዮጵያ አርቲፊሻል ኢንተለጀንስ ኢንስቲቲዩት ውስጥ የሶፍትዌር ዲቨሎፐር በመሆን ይሰራል። እርሱና የሙያ ባልደረቦቹ በሳይንስ ሙዚዬም ውስጥ "የፊንቴክ" ወይም በፋይናንስ ዘርፍ ላይ የሚገኝ ቴክኖሎጂን ይዘው ቀርበው ለጎብኚዎች የማስተዋወቅ ስራን እየሰሩ ይገኛሉ።

"የፋይናንስ ቴክኖሎጂው 'ማይክሮ ሎን' ይባላል። ከዚህ ቀደም የቢዝነስ ሃሳብ ኖሯቸው የብድር አገልግሎት ያለ ማስያዣ ለማግኘት የሚቸገሩትን የስራ ፈጣሪዎች ችግር የሚያቃልል ነው" የሚለው ወጣት ኤፍሬም፣ በሰው ሰራሽ አስተውሎት አማካኝነት የተጠቃሚዎችን ሙሉ መረጃ በማስገባትና ከአበዳሪ ባንኮች ጋር በማቀናጀት፣ የተበዳሪውን ቀደምት የብድር ታሪክ በማጥናት፣ ያለውን ገቢና የመመለስ አቅም በማቀናጀት በሰው ሰራሽ አስተውሎት ቀመር አማካኝነት ተበዳሪው ያለምንም መጉላላት እምነት አግኝቶ የስራ ማስኬጃውን እንዲያገኝ እንደሚያስችል ይናገራል። በዋናነት ይህ ቴክኖሎጂ ትክክለኛውን መረጃ ለአበዳሪ አካላት እንዲሰጥ እንደሚያስችል ይገልፃል።

"የቢዝነስ ወይም የስራ ሃሳብ ያላቸው ሰዎች የስራ ማስኬጃ ለማግኘት ወደ ባንኩ መጥተው ብድር ይጠይቃሉ" የሚለው ወጣት ኤፍሬም፣ በኢትዮጵያ አርቲፊሻል ኢንተለጀንስ ኢንስቲቲዩት የተሰራው ይህ ቴክኖሎጂ ፕሮጀክቱን በማጥናትና አዋጪነቱን በመለካት ተጠቃሚዎች ብድር ማግኘት እንዲችሉ ምክረ ሃሳብ እንደሚሰጥ ይናገራል።

የኢትዮጵያ አርቲፊሻል ኢንተለጀንስ ኢንስቲቲዩት የሶፍትዌር ዲቨሎፐሩ ወጣት ኤፍሬም እንደሚለው፤ «ሰው ሰራሽ አስተውሎት" (አርቲፊሻል ኢንተለጀንት) እንደ ሰው ማስተዋል የሚችሉ የኮምፒውተር ፕሮግራሞችን ወይም ማሽን መተግበሪያዎችን የመፍጠር የሳይንስ እና የምህንድስና ዘርፍ ነው። የመጨረሻው ጥረት በዓለም ዙሪያም ሆነ በሰው ልጆች አኗኗር ላይ ያተኮሩ ችግሮችን ለመፍታት እና ግቦችን ለማሳካት የሚያስችሉ የኮምፒውተር ፕሮግራሞችን መፍጠር ነው።

ሰው ሰራሽ አስተውሎት የኮምፒውተር ፕሮግራሞች ወይም በኮምፒውተር ፕሮግራም የሚደረጉ ማሽኖች ከመረጃ እንዲማሩ፣ ከአዳዲስ ግብዓቶች ጋር እንዲላመዱ እና የሰው መሰል ተግባሮችን እንዲያከናውኑም ያስችላል። ኢትዮጵያም በዘርፉ ውጤታማ ስራዎችን ለማከናወን የሚያስችላትን ምርምሮች እያደረገች እንደሆነ ጠቅሶ፣ በሳይንስ ሙዚዬም ውስጥ የቀረቡትን ስራዎች ለእዚህ እንደ አብነት መጥቀስ ይቻላል።

"የማሽን ወይም የኮምፒውተር ፕሮግራም የማሰብ እና የመማር ችሎታ ነው። የሰው ስራሽ አስተውሎት ጽንሰ ሀሳብ የተመሠረተው እንደ ሰዎች ማሰብ፣ መማር እና የተለያዩ ተግባራትን ማከናወን ችሎታ ያላቸውን ማሽኖችን በተለይም የኮምፒውተር ፕሮግራሞችን በመገንባት ሀሳብ ላይ የተመሠረተ ነው" የሚለው ወጣት ኤፍሬም፣ ይህንን ሃሳብ የእነርሱ ዲቪዥን "የማይክሮ ሎን" ብድር ወደሚፈቅድ ቴክኖሎጂ በመቀየርና በማላመድ በዘርፉ የሚፈጠሩ ችግሮችን ለመፍታት የሚያስችል ምርምር ለማድረግ እንዳገዛቸው ይናገራል።

እንደ ወጣት ኤፍሬም ገለፃ፤ በኢትዮጵያ ውስጥ የፋይናንሺያል ቴክኖሎጂ "ፊንቴክ" ዘርፍ ከጊዜ ወደጊዜ እያደገ ይገኛል። ይህን እድል ወጣቶች፣ ኢኖቬተሮችና ሰፊ የስራ እድል መፍጠር የሚችሉ የቢዝነስ ሰዎች እንዲጠቀሙበት ለማስቻል የኢትዮጵያ አርቲፊሻል ኢንተለጀንስ ኢንስቲትዩት የምርምር ስራዎችን በማድረግ አዳዲስ ቴክኖሎጂዎችን በማስተዋወቅ ላይ ይገኛል።

ወጣት ኤፍሬም በተለይ ለዝግጅት ክፍላችን አስተያየቱን ሲሰጥ "የሰው ልጆች የተለያዩ ተግባሮችን ማከናወን እና አብዛኛውን ጊዜ የሰውን የማሰብ ችሎታ የሚጠይቁ ችግሮችን መፍታት የሚችሉ የኮምፒውተር ፕሮግራሞችን መስራት በዚህ ዘመን አስፈላጊ ነው" በማለት ከዚህ ቀደም በነበረው የተለምዶ አሰራር እንደ የእይታ ግንዛቤ፣ የንግግር ማወቂያ፣ የውሳኔ አሰጣጥ እና የቋንቋ ትርጓሜ ያሉ ነገሮች በመደበኛነት የሰውን የማሰብ ችሎታ የሚፈልጉ ሁሉም ነገሮች ነበሩ ይላል። አሁን ግን የኮምፒውተር ፕሮግራሞች እነዚህን ተግባራት ለመፍታት የማሰብ ችሎታቸውን እንደሚጠቀሙ ይገልፃል። እነርሱ የሚሰሩበት "የማይክሮ ሎን" ፋይናንሺያል ቴክኖሎጂም የሰው ልጆችን ሚና በመተካት ፍትሃዊና ከአድሏዊ አሰራር የፀዳ እንዲሆን እንደሚያስችል ነው የሶፍትዌር ዲቨሎፒንግ ባለሙያው የሚያስረዳው።

### እንደ መውጫ

አርቲፊሻል ኢንተለጀንስ የሚለው ቃል እንደ አውሮፓውያን አቆጣጠር በ1956 የተፈጠረ መሆኑን መረጃዎች ያመለክታሉ። ኢትዮጵያ ውስጥ ይህን ፅንሰ ሃሳብ መሬት ላይ አውርዶ ተግባራዊ የቴክኖሎጂ ፈጠራዎች ምርምር ማድረግ ከተጀመረ ጥቂት ዓመታትን ነው ያስቆጠረው። ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በዓለማችን ላይ የሰው ሰራሽ አስተውሎቶች በተለያዩ የቴክኖሎጂ ውጤቶች አማካኝነት እየተወሳሰቡ እና እየተከማቹ በመጡ የኢንተርኔት መረጃዎች ክምችት፣ የላቁ ስልተ ቀመሮች እና ኮምፒውተሮች መሻሻሎች አማካኝነት እየዘመኑና ይበልጥ ውጤታማ እየሆኑ መጥተዋል።

ዓለም በቴክኖሎጂው በተለይ በሰው ሰራሽ አስተውሎት (አርቴፊሻል ኢንተለጀንስ) ዘርፍ እጅግ የረቀቀና የዘመነ ደረጃ ላይ ትገኛለች። ሉላዊነት የፈጠረው ትስስር ቴክኖሎጂ በፍጥነት እንዲያድግና ብዙ ሺህ ኪሎ ሜትሮች የበራችን ደጃፍ የቀረቡን ያህል እንዲሰማን እያደረገ ይገኛል። ምድራችንን ይፈትኑ የነበሩ ውስብስብ ችግሮች አሁን በአስደናቂ የፈጠራ ውጤቶች መፍትሄ እያገኙ ነው።

አገራት የንግድ፣ የዲፕሎማሲና ሌሎች መሰል ትስስሮችን በዲጂታል ቴክኖሎጂ (በይነ መረብ) ያደርጋሉ። ይህ ጊዜን፣ ጉልበትን፣ ከፍተኛ ወጪንና የተዛባ አሰራርን ከማስቀረቱም በላይ ደህንነትንና አስተማማኝነትን ማረጋገጥ አስችሏል። በመግቢያችን ላይ እንዳነሳነው ቴክኖሎጂና ሳይንሳዊ ምርምር በሰው ልጅ አቅም የማይታሰቡትን ሁሉ እንዲተገበሩ፣ ረቂቅና ሚስጥራዊ የሆኑ ትንግርት የሚመስሉትን እውን እንዲሆኑ ያስቻለ ነው።

ኢትዮጵያም በዚህ ሰፊ የቴክኖሎጂ ባህር ውስጥ መልህቋን መጣል እንድትችል ወጣቱ ትውልድ ራሱ ከሚያደርገው ጥረት ባሻገር ምቹ አጋጣሚ እንዲፈጠርለት ይሻል። እንደ ሳይንስ ሙዚየም አይነት የመሰረተ ልማት ግንባታዎችና ሌሎች ድጋፎች ደግሞ ሂደቱን በእጅጉ እንደሚያፋጥኑት ይታመናል።

# ወቅታዊ ትንታኔ

# በአንድ ሀገር ሁለት መከላከያ ሰራዊት ይቻላልን?

ክፍለዮሐንስ አንበርብር

የአሸባሪ የሕወሓት ቡድን ከሁለት ዓመት በፊት በሰሜን ዕዝ ላይ ጥቃት ከፈፀመ በኋላ ራሱን እንደ ሀገር መከላከያ መቁጠር ጀምሮ ነበር። እንደ አንድ የሀገር መከላከያ ሰራዊት ራሱን በመቁጠርም በታጠቁ ኃይሎች አማካይነት ከፍተኛ ጉዳት አድርሷል። ጦርነቱ ከተከፈተ ጀምሮ ‹‹የትግራይ መከላከያ ሰራዊት ነኝ›› ብሎ ራሱን የሰየመው አካል፤ የባህርዳር አየር ማረፊያን በሮኬት በመምታት አገልግሎቱ እንዲስተጓልና ከጥቅም ውጭ እንዲሆን እንዲሁም በጥቃቱ ንፁሃን ዜጎችም ሰላባ እንዲሆኑ ማድረጉ ይታወሳል።

አሸባሪው ቡድን ወደ ጎንደርም በተደጋጋሚ ሮኬቶችን በመተኮስም በንብረት ላይ ከፍተኛ ጉዳት ያደረሰ ሲሆን፣ ሰብዓዊ ጉዳትም ማስከተሉ ይታወቃል። በዚህ ብቻ ሳይሆን ጎረቤት ሀገር ኤርትራን በመተንኮስም ወደ አስመራ ከተማ ሮኬት በመተኮስ ጉዳት ማድረሱ የሚታወስ ነው።

ታዲያ አሸባሪው ሕወሓት ራሱን ‹‹የትግራይ መከላከያ ሰራዊት›› ብሎ መሰየምና ህገ መንግስታዊ እንድምታው፣ ከሀገር መከላከያ ሰራዊት የዘረፋቸው የጦር መሳሪያዎችና ዕጣ ፋንታቸው፣ የሕወሓት አካሄድና ፌደራል ሥርዓቱ ላይ የደቀነው አደጋና በቀጣይ ሊያመጣቸው የሚችለው መዘዝ ብሎም መወሰድ ስለሚገባቸው መፍትሄዎች የህግ ባለሙያዎች ሙያዊ ሐሳባቸውን ይሰጣሉ።

በዋቻሞ ዩኒቨርሲቲ የህግ መምህር እና ጠበቃ አቶ ፀጋዬ ደመቀ እንደሚሉት፤ በአንድ ሉዓላዊ ሀገር ውስጥ በማናቸውም መስመር ሊኖር የሚችለው አንድ የሀገር መከላከያ ሰራዊት አደረጃጀትና የሀገሪቱ የበላይ አመራር ነው። ከዚህ በዘለለ በአንድ ሀገር ሁለት ዓይነት አቋም ያለው የሀገር መከላከያ ይኖራል ብሎ መጠይቅ በራሱ ግራ የሚያጋባ ነው። ጥያቄውን መጠየቅ ብቻ ሳይሆን እንደዚህ የመሆን ዕድል አለው ብሎ ማሰብ በራሱ ስህተት ነው የሚል እምነት አላቸው።

በየትኛውም ሀገር አንድ የሀገር መከላከያ መኖር አለበት። በዓለም ነባራዊ ሁኔታም እየሆነ ያለውም ይኸው ሃቅ ነው። ይህም በመሆኑ በማናቸውም መመዘኛ በአንድ ሀገር የሚኖረው የሀገር መከላከያ ሰራዊት የሀገሪቱ ሉዓላዊ ጠባቂና ከጦር ኃይል ሁሉ ቅድሚያ የሚሰጠው ነው። የሕወሓት ቡድን የሰሜን ዕዝን በማጥቃት የዘረፋቸውን የጦር መሳሪያዎች ይዞ የትግራይ መከላከያ ሰራዊት ብሎ ራሱን መሰየሙ በብዙ መንገድ አግባብነት የጎደለው ስለመሆኑና ከሞራልም ሆነ ከህግ አግባብ አንፃር ዋጋ ቢስ ስለመሆኑም ያብራራሉ።

የሽብር ቡድኑ የሰሜን ዕዝ ላይ ጥቃት በመክፈት የዘረፈው ሃብት የመላ ኢትዮጵያን ሃብት እንጂ የተወሰነ ቡድን ሃብት አለመሆኑን መረዳት ይገባል። ይህ የጦር መሳሪያ ሲገዛ ኢትዮጵያ ከሃብቷ ላይ በመቀነስ የተለያዩ ድርድሮችን በማካሄድና ሚስጥራዊ ሰነዶችን በመለዋወጥ የፈፀመችው እንጂ ዝም ብሎ እንደተራ ሸቀጥ ከየትም የተሸመተ አይደለም። እነዚህ የጦር መሳሪያዎች እና ማሽነሪዎች ሀገርን እና ህዝብን ለመጠበቅ እንጂ ለተወሰኑ ቡድኖች ፍጆታ አሊያም ግልጋሎት የተገዙ አለመሆኑም የአደባባይ ሃቅ ነው። ዳሩ ግን በሰሜኑ የሀገሪቱ ክፍል የነበረው ከፍተኛ የጦር መሳሪያ ለመጠቀም እና የፌደራል መንግስቱን ለማንበርከክ ሲባል ብቻ በዝርፊያ በተገኘ የጦር መሳሪያ አንድን ቡድን ራሱን እንደ መከላከያ ሰራዊት መቁጠር አግባብ እንዳልሆነም ይገልፃሉ።

የፌደራል መንግስትም የአሸባሪ ቡድን በተለያዩ አጋጣሚዎች ወደ እጁ ያስገባቸውን የጦር መሳሪያዎችን ‹‹መልስ›› ማለት ህጋዊም ሆነ ሞራላዊ መብት አለው። ለዚህም የሚከለክለው አንዳች ነገር የለም ባይ ናቸው። ይህ የጦር መሳሪያ ሲገዛ ኢትዮጵያን ከጠላት ለመጠበቅ እንጂ በሀገር ውስጥ ያለ አንድ ቡድን ታጥቆ ሌላው እንዲያጠቃ መሆን የለበትም። ሕወሓትም ከሰሜን ዕዝ በመዝረፍ የታጠቀውን የጦር መሳሪያ ለፌደራል መንግስት መመለስ እንደሸንፈት ሳይሆን ሕግን ከማስከበር አኳያ ማየት ይኖርበታል።

እንደ አቶ ፀጋዬ ገለፃ፤ ይሁንና ‹‹መሳሪያው ለመንግስት ከመለስኩ እጠቃለሁ።›› የሚል እሳቤ ቢኖር እንኳን በፖለቲካዊ ውሳኔ የሚስተካከል እንጂ መሳሪያውን ታጥቄ ራሴንም እንደአንድ ሉዓላዊ ሀገር የጦር መከላከያ ሰራዊት በመቁጠር እሄዳለሁ የሚለው እሳቤ አግባብ አይሆንም። በማናቸውም መስፈርት ነገሮችን ለማስተካከል የሚቻለውም በጦር መሳሪያ ጋጋታ እና በጉልበት ሳይሆን ህግ፣ ፍትህ እና ርትዕን ባማከለ መልኩ መሆን አለበት ይላሉ።



አቶ ፀጋዬ ደመቀ

> **አሸባሪው ሕወሓት በበርካታ ምክንያቶች አመጣጡና አካሄዱ አደገኛ ነው። በመሆኑም በቀጣይም የፌደራል መንግስት ብቻ መታጠቅ ያለበትን መሳሪያ ሕወሓት ታጥቆ መቀጠል አይችልም**



አቶ ኑሩ መኩሪያ

ከህገ መንግስቱ አኳያ ሲመዘን ደግሞ የሕወሓት ቡድን የታጠቀው መሳሪያ እና አሁን ያለው ቁመና ለሀገር ሉዓላዊነት አደገኛ እንደሚሆን አመላካች ነው። በመሆኑም የሀገሪቱ የህጎች ሁሉ የበላይ የሆነውን ህገ መንግስት ማክበር አስፈላጊ ነው። ይህም በመሆኑ በቡድኑ እጅ የገቡ የሀገር መከላከያ የጦር መሳሪያዎችን ለሀገር ጠባቂ የሆነው አካል ወይንም ባለቤቱ መመለስ ህገ መንግስቱን ከማክበር እንጂ ከሽንፈት መቆጠር የለበትም የሚል አቋም አላቸው የህግ ባለሙያው- አቶ ፀጋዬ።

የሀገሪቱን ህገ መንግስት ዋቢ የሚያደርጉት አቶ ጸጋዬ፤ ‹‹በህገ መንግስቱ አንቀፅ 87 የመከላከያ መርሆች በሚለው መዘርዝር ሥር፤ የሀገሪቱ የመከላከያ ሰራዊት የብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ህዝቦች ሚዛናዊ ተዋጽኦ ያካተተ ስለመሆኑ፣ የመከላከያ ሚኒስትር ሆኖ የሚሾመው ሲቪል ስለመሆኑ፣ የመከላከያ ሰራዊት የሀገሪቱን ሉዓላዊነት ከመጠበቅ በተጨማሪ በህገ መንግስቱ መሰረት አስቸኳይ ጊዜ የሚሰጡትን ተግባራት ያከናውናል፣ የመከላከያ ሰራዊቱም ማናቸውም ጊዜ ለህገመንግስቱ ተገዥ ይሆናል፣ የመከላከያ ሰራዊት ተግባሩን ከፖለቲካ ድርጅቶች ወገናዊነት ነፃ በሆነ አኳኋን ያከናውናል›› ይላሉ። ይህ ማለት ደግሞ በአንድ ሀገር ውስጥ የሉዓላዊነት ጠባቂ የሀገር መከላከያ ሰራዊት ስለመሆኑ በደንብ ያስረዳል ባይ ናቸው። ታዲያ ከዚህ አኳያ መረዳት የሚቻለው የሀገሪቱን ሉዓላዊነትና ዳር ድንበር መጠበቅ በዋናነት የሀገር መከላከያ ሰራዊት እንጂ የክልሎች ዋነኛ ሚና አለመሆኑን ማጤን ይገባል። ለዚህም የፌደራል መንግስት በትጥቅና በሌሎችም የተሻለ ሆኖ መደራጀትና ሌሎችም እንደ አስፈላጊነቱ መታጠቅ የሚችሉበት አሰራር መዘርጋት አለበት። ሆኖም በማናቸውም መንገድ የሀገር መከላከያ ሰራዊትን የሚገዳደር አካል ከተፈጠረ ሀገር አትፀናም ይላሉ።

በሰመራ ዩኒቨርሲቲ የህግ መምህርና ጠበቃው አቶ ኑሩ መኩሪያ በበኩላቸው፤ በአንድ ሀገር ውስጥ የተለያዩ የሰራዊት አደረጃጀቶች ሊኖሩ የሚችሉበት አጋጣሚ ስለመኖሩ ይጠቁማሉ። በተለይም የፌደራል ሥርዓትን በሚከተሉ ሀገራት እንደ ተጨባጭ ሁኔታው የሰራዊት አደረጃጀቶች ይፈጠራሉ። ስለዚህ ከአንድ በላይ የታጠቀ አካል ይኖራል ወይ የሚል ሃሳብ ከመጣ አዎ ይኖራል የሚለው ሐሳብ ገዥ ይሆናል፤ ይሁንና ለምን ዓላማ እና በማን ኃላፊነት ነው የሚለው ግንዛቤና ግልጽነት ሊኖረው ብሎም ምላሽ የሚሰጠው ህጋዊ ጉዳይ ነው ይላሉ።

የፌደራል ሥርዓቱ በሚፈቅደው መንገድ ክልሎች የየራሳቸው አደረጃጀት እና የሰራዊት ግንባታ ያካሂዳሉ። ለምሳሌ የኢትዮጵያ ሕገ-መንግስት በሚፈቅደው መንገድ ክልሎች የየራሳቸውን የፖሊስ ሰራዊት አደራጅተዋል፤ ለሚፈለገው ዓላማው እየተገለገሉ ነው። ሆኖም የአንድ ሀገር ሉዓላዊነት የሚጋፋ አደረጃጀት ግን አግባብነት የለውም።

ይሁንና የአሸባሪው የሕወሓት ቡድን አካሄድ በርካቶች የማያውቁትና ብሎም የሀገሪቱን ሕገ መንግስት የተቃረነ አካሄድ ነው። ይህም በመሆኑ የሌሎች ክልሎች የፖሊስ አባላት ያልታጠቁትን የጦር መሳሪያ በሰፊው የታጠቀ እና በሰው ኃይል አደረጃጀቱም ለኢትዮጵያ ስጋት በሚሆን ደረጃ የተዋቀረ ስለመሆኑ ያብራራሉ። በአሁኑ ወቅትም ኢትዮጵያ የገባችበት ቀውስ አሸባሪው ሕወሓት ተጠያቂ መሆኑንና ይህም የሀገር መከላከያ ሰራዊትን የሚገዳደር አደረጃጀት፣ ሎጂስቲክስና የሰው ኃይል የማፍራትና የማሰልጠን ዕድል በማግኘቱ እንደሆነም የህግ ባለሙያው አቶ ኑሩ ያመለክታሉ።

ኢትዮጵያን በመሰሉ ሀገራት፤ የፌደራል መንግስቱ በማናቸውም ሁኔታ የበለጠ የታጠቀና የሰለጠነ መሆን አለበት። ይህም ሀገር እንደ ሀገር መቀጠል የምትችልበትን እድል ለመፍጠር ነው። በአንድ ሀገር ውስጥ ሉዓላዊነትን ለአደጋ የሚጥል አካል ወይንም የታጠቀ ቡድን መሳሪያውን መፍታት ግድ ይለዋል። በአንድ ሀገር ውስጥ የሀገር መከላከያ ሰራዊትን የሚገዳደር ሰራዊት የገነባ አካል አደገኛ ስለሚሆን፤ በማናቸውም አግባብ መስተካከል አለበት የሚል ሐሳብ አላቸው።

ሕወሓት የትግራይ ውጭ ግንኙነት በሚል አዲስ አደረጃጀት የፈጠረ ሲሆን፣ ይህም አግባብ አለመሆኑን ነው አቶ ኑሩ የሚስረዱት። በሕገ መንግስቱ አንቀፅ 86 ላይ የውጭ ግንኙነት መርሆች በሚለው ሥር የኢትዮጵያ ህዝቦችን ጥቅም የሚስያጠብቅና የሀገሪቱን ሉዓላዊነት የሚያስከብር የውጭ ግንኙነት ፖሊሲ ማራመድ፣ የመንግስታትን ሉዓላዊነትና እኩልነት ማክበር፣ በሌሎች ሀገራት ጉዳዮች ውስጥ ጣልቃ አለመግባት፣ የሀገሪቱን የውጭ ግንኙነት ፖሊሲ በጋራ ተጠቃሚነትና በእኩልነት ላይ የተመሰረተ መሆኑን እንዲሁም በዓለም አቀፍ ደረጃ የሚደረጉ ስምምነቶች የኢትዮጵያን ጥቅም የሚስከብሩ መሆናቸውን ማረጋገጥ፣ የኢትዮጵያን ሉዓላዊነት የሚያስከብሩና የህዝቦቿን ጥቅም የማይፃረሩ ዓለም አቀፍ ህጎችና ስምምነቶችን ማክበር፣ ከጎረቤት ሀገሮችና ከሌሎች የአፍሪካ ሀገሮች ጋር በየጊዜው እያደገ የሚሄድ ኢኮኖሚያዊ ህብረትና የህዝቦች አቶ ኑሩ መኩሪያ ወንድማማችነትን ማጎልበት፣ በሀገሮች መካከል የሚነሱ ግጭቶች ሰላማዊ በሆነ መንገድ እንዲፈቱ ጥረት ማድረግ ሲሆን፤ ይህንን በዋናነት የሚመራው የኢትዮጵያ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ይሆናል። ዳሩ ግን አሸባሪ ሕወሓት ትግራይ የኢትዮጵያን ሉዓላዊ ግዛት አካል ሆና ሳለ የትግራይ የውጭ ግንኙነት ብሎ መመስረቱም አግባብነት የጎደለውና ቡድኑ ለህጎች የማይገዛ ስለመሆኑም ያብራራሉ።

አሸባሪው ሕወሓት በበርካታ ምክንያቶች አመጣጡና አካሄዱ አደገኛ ነው። በመሆኑም በቀጣይም የፌደራል መንግስት ብቻ መታጠቅ ያለበትን መሳሪያ ሕወሓት ታጥቆ መቀጠል አይችልም። ይሁንና ግን አሸባሪ ቡድን ክላሽና ቀላል መሰል መሳሪያዎችን መፍታት አለበት ብሎ መከራከር ውሃ አይቋጥርም፤ ምክንያቱ ደግሞ እነዚህን የመሰሉ መሳሪያዎችን አርሶ አደሩ እጅም ገብተዋልና ነው። ሆኖም የሚታጠቀው የጦር መሳሪያ መጠንና ዓይነት ሊወሰንለት እንደሚገባም ነው የሚያስረዱት። ይህም በህግና በአዋጅ የሚደነግግ መሆን እንዳለበት ያስረዳሉ። የሕወሓት አደገኛ አመጣጥና አካሄድም በሌሎች ቡድኖች እንዳይደገም የፌደራል መንግስት ጥንቃቄ ማድረግ እንዳለበትም ይመክራሉ።

ምሁራኑ እንደሚሉት፤ በአንድ ሀገር ውስጥ የተለያዩ የሰራዊት አደረጃጀት ቢኖርም የሀገር ዳር ድንበርን በመጠበቅና ሉዓላዊነት በማስከበር ረገድ በዋናት ኃላፊነቱን የሚወስደው የሀገር መከላከያ ሰራዊት ነው። ይህ በመሆኑም በአንድ ሀገር በበላይነት የሚደራጀው የሀገር መከላከያ ሰራዊት የሚያደራጀው የሰው ኃይል፣ የሚሰለጥንበት ታክቲክና ክህሎት፣ የሚመደብለት በጀት፣ የሚፈጽማቸው ተልዕኮዎች ብሎም የሚሰጠው ኃላፊነት የላቀ ይሆናል። ይህንንም በዋናነት የሚፈጽመው የሀገር መከላከያ ሰራዊት ይሆናል።

በርካታ ሀገራትም ይህን በህገ መንግስታቸው፣ በመንግስታቸው አሰራርና በአስተዳደራቸው በህግ፣ አዋጅ፣ በመመሪያ ይደግፉታል፤ ይተገብሩታልም። ይሁንና ከዚህ በዘለለ የሀገሪቱን ሉዓላዊ ሀገርን የሚገዳደር ኃይል የተፈጠረ እንደሆነ ሰብዓዊ እና ዴሞክራሲያዊ ጥሰቶች ከመፈፀምና ከመበራከት በዘለለ ሽብርተኝነትና ያልተረጋጋ ሀገር የሚፈጥር ይሆናል የሚል ምክር ሐሳብ አላቸው። በመሆኑም የሀገር ሉዓላዊነትን ለመጠበቅ በአንድ ሀገር ውስጥ መኖር ያለበት አንድ የሀገር መከላከያ ሰራዊት ብቻ መሆን አለበት ባይ ናቸው።

ማህበራዊ

# ሴቶች

# ጠላትን ያንበረከኩ ጀግና እንስቶች

**ጽጌረዳ ጫንያለው**

የጦርነት ወሬ ሸው ሲል ቅድሚያ ተጠቂዋም ተጎጂዋም ሴት እንደሆነች ሁላችንም እንስማማለን። ነገር ግን ጀብዱ ፈጻሚነቷን ለመቀበልና ለመናገር አንደበታችን ይያዛል። ስለጀግንነትና ጀብዱ ሲነሳ ሴቷ ትዘነጋለች። ለዚህ ደግሞ ዋነኛ ምክንያቱ ሚዛናዊ የሆነ አመለካከት ስለሌለን ነው። ግን ዞር ካልን ከየትኛውም ጦርነት ጀርባ ሴቶች አይጠፉም። ያለእነርሱ ብልሃትና ድጋፍ ወንድ ልጅ ቀድሞ መውጣት አይችልም። ያለእነርሱም ምሪት እንዲሁ መላቁ አይመጣም። ማሸነፍ ሁሉ የሚቻለው በእነርሱ ድጋፍ ብቻ እንደሆነ ብዙ ማሳያዎችን ማንሳት እንችላለን። አንዱ እቴጌ ጣይቱ ናት። ምኒልክና መሰል የአገር ባለውለታዎች ብቅ ያሉት ጣይቱ በሰጠችው አመራርና እንቢ አልገዛም ባይነት ነው።

ዛሬም ቢሆን ከወንዶች በላይ ታሪክ ሰርተው የሚነሱ በርካቶች ናቸው። በተለይም ከሕወሓት ጋር በነበሩት ጦርነቶች ጠቅሰን የማንጨርሳቸው በርካታ የመከላከያ ሰራዊት ሴት ጀግኖች አሉን። ከእነዚህ መካከል ለዛሬ ቀደም ሲል በአዲስ ዘመን ጋዜጣ ከዘገብናቸው ጥቂቶችን ልናስታውሳቸው ወደናል።

በሙያ፣ አልሞ በመተኮስ፤ ብቁ ሴት ጀነራል መኮንን በመሆን፣ ተራራና ሸንተረሩን ዱርና በረሃው ሁሉ አቋርጠው በመሄድና ተፈጥሮ ሳያግዳቸው አሸናፊ ሆነው በማሳየት አጀብ ያሰኙን ናቸው እነዚህ አባላት። ከዚያም ባሻገር ስንል ለሌሎች ሴቶች የሥነልቦናቸው ጥንካሬ ማሳያ ሆነዋል። ታሪክም አስመዝግበዋል። እርግጥ ነው ምስጢሩ አንድና አንድ ነው።

እነአርበኛ ሸዋረገድ ገድሌ ሉዓላዊነትን የደፈረ ማንነትን ሊያጠፋ የተነሳ የውጭ ወራሪን ለመመከት በብዙ ነገር ተፈትነው ያልወደቁና ለአገራቸው የተዋደቁ መሆናቸውን አስመስክረዋል። ሀገር መውደድን፣ ለዓላማ ጸንቶ ማሸነፍን አስተምረው ያለፉ ታላቅ ሴትም ናቸው። በአምስት ዓመቱ የፋሽስት ኢጣሊያ ጦር ወረራ ኢትዮጵያ ለተቀዳጀችው ድል አይተኬ ሚና ተጫውተዋልም። ምክንያቱም በጦርነቱ ወቅት መረጃ በማቀበል፣ መድኃኒት በመላክ እና መሣሪያ በመግዛት የማይተካ ሚና ነበራቸው።

ሸዋረገድ ተክሌ 12 ጊዜ ታስረው የተፈቱ፣ እስከ ሞት ፍርድ የተፈረደባቸው ነገር ግን ወደ እድሜ ይፍታሽ የተቀየረላቸው አርበኛ ሆነው ለዛሬዎቹ ምሳሌ ሆነዋል። ታዲያ የዛሬዎቹስ ለምን አይሆኑም? ይሆናሉ እንጂ። ደግሞም ሆነውም አሳይተዋል። ከእነዚህ መካከል ምክትል አስር አለቃ ገበያነሽ ደባልቄ አንዷ ነች። እርሷ ከሀዲውን ጁንታ ኮሎኔል ማንቁርቱን ይዛ ያስረከበች ሴት ናት። ኮሎኔሉ 20ኛ ቃሉ ክፍለ ጦር ሰሜን ዕዝ ካሏት የጦር ክፍሎች ውስጥ አንዱ ሲሆን፤ በዚህ ክፍለ ጦር 1ኛ ብርጌድ 1ኛ ሻለቃ አባል የሆነችው ምክትል አስር አለቃዋ የሻለቃው አዛዥ ኮሎኔል ሰለሞን ገ/ዮሃንስ አጃቢ ነች። ጁንታ መሆኑን ግን አታውቅም።

ኮሎኔሉ በሰሜን ዕዝ ላይ ክህደት ከመፈጸሙ ከሶስት ቀን በፊት ሰራዊቱ የምግብና መጠጥ አገልግሎት የሚያገኝባቸውን መንገድ በመዝጋት ሰራዊቱን ለከፍተኛ ርሃብና ጥም ዳርጎታል። ሁሉም የሰራዊት አባል የግል ትጥቁን በአንድ ክፍል በማስቀመጥ በህብረተሰብ የድጋፍ ሥራዎች ላይ እንዲረባረብ ማድረጉንም ታስታውሳለች። በተለይም ጥቅምት 24 ቀን 2013 ዓ.ም ምሽት ላይ ሁሉንም የጥበቃ ቦታዎች በትግራይ ተወላጅ የሰራዊት አባላት እንዲሸፈኑ በማድረግ፣ የከሃዲው ቡድን ልዩ ኃይልና ሚሊሻ ምንም አይነት ዝግጅትና ትጥቅ ባልነበረው ሰራዊታችን ላይ ከፍተኛ ተኩስ እንዲከፍትም አድርጓል። ሆኖም ታላቅ ጀግንነትና ኢትዮጵያዊ ማንነትን የወረሰው ጀግናው ኃይላችን የማይታሰቡ ጀብዶችን ጭምር በመፈፀም፣ ወደ ኤርትራ ስልታዊ ማፈግፈግ በማድረግ ራሱን ማዳን እንደቻለ ትናገራለች።

በዚህ ሁሉ ግፍና በደል መሃል የሻለቃዋ ዋና አዛዥ ኮሎኔል ሰለሞን ገ/ዮሃንስ ራሱን መፀዳጃ ቤት ውስጥ በመደበቅ በጁንታው የተሰጠውን ተልዕኮ መፈፀም እንደጀመረ በሃዘን ስሜት ውስጥ ሆና ታስውሳለች።

‹‹ውትድርና በኢትዮጵያዊነት ፍቅር መታጠብና በጀግንነት ካባ መድመቅ ነው›› የምትለው እንስቷ ጀግና ፤ ራስህን ለሀገር አሳልፈህ ከሰጠህ ኢትዮጵያዊ መሆን ብቻውን ጀግንነትን ይወልዳል ባይ ነች። ምክንያቷም የቀድሞ አለቃዋን እንዴት ከስሯ እንዲንበረከክ እንዳደረገችው አይታበታለችና ነው። ሁኔታውን ስታስረዳ “… ሰራዊታችን በታፈነበት ጥቅምት 24 ምሽት 2 ሰዓት ላይ በከባድ መሳሪያ የታጀበ ተኩስ ወደ ካምፓችን ተተኮሰ፣ በዚህ ሰዓት ወደ መፀዳጃ ቤት ራሱን የደበቀው ከሃዲው አዛዥ ተብዬ ፣ እኔ በትግራይ ሚሊሻና ልዩ ሃይል ጥይት ከምሞት አንተን ገድዬ ራሴን አጠፋለሁ አልኩት፣ ተኩሱ በርትቷል፣ ሁሉም ራሱን ለማዳን ወደህሊናው የመጣለትን አማራጭ እየተጠቀመ ይሯሯጣል…”

“… በመጨረሻም ከተደበቀበት መፀዳጃ ቤት እንዲወጣና እኔ የምለውን ብቻ እንዲፈፅም እሽ የማይል ከሆነ ግን እንደምገድለው አስጠነቀቁኩት፥ እሱም በፍርሃት ውስጥ ሆኖ ከተደበቀበት ቦታ ወጥቶ ወደነገርኩት ቦታ መጣ፥ ሽጉጡንና ማዕረጉን እንዲሰጠኝ አደረኩ፣ ከዛም ጫማውን እንዲያወልቅ አድርጌ በየመንገዱ ከማገኛቸው የሰራዊት አባላት ጋር በመተባበርና ሙሉ ሌሊት የእግር ጉዞ በማድረግ ኤርትራ ይዤው በመግባት ታማኝ እና ሙሉ ኢትዮጵያዊ ለሆኑ አመራሮች አስረከብኩ።” በማለትም ሰራዊታችን በራሱ ወገኖች የደረሰበትን በቃላት የማይገለፅ ግፍና በደል ተሸክሞ ቂምን ሳይሆን ኢትዮጵያዊ ፍቅር አስቀድሞ ለድል በመብቃቱ ከፍተኛ ደስታ እንደተሰማትም ምክትል አስር አለቃ ገበያነሽ ደባልቄ ስሜቷን አጋርታለች።

ኢትዮጵያችን ምንም እንኳን በጉያዋ ተወሽቀው ሳቋን እየቀሙ ውርደቷን የሚያፋጥኑና መበተኗን ገሃድ ለማውጣት ሌት ተቀን የሚሯሯጡ ወጪት ሰባሪዎች ቢኖሩም፣ ክብሯን የሚያስጠብቁ ከራሳቸው ሕይወት ይልቅ የሀገራችውን ክብር የሚያስቀድሙ፣ የማይታመን ጀግንነት እየፈፀሙ ኢትዮጵያችንን ከፍ ያደረጉ የበርካታ የቁርጥ ቀን ልጆች መሆኗን ካስመሰከሩት መካከል ሌላኛዋ ሴት ወታደር ገነት ዮሀንስ ናት።

ገነት ገና ልጅ እያለች ነው የውትድርና ፍቅሩ ያደረባት። ለዚህም ማሳያው ሁልጊዜ ከትምህርት ቤት ስትመለስ ወታደራዊ ሰላምታ ለእናቷ በማቅረብ ነበር ወደቤት የምትገባው። ከዚያም ህልሟን እውን ለማድረግ አስረኛ ክፍል ተፈትና የውትድርናን መንገድን ምርጫዋ አደረገች። ይህ ሲሆንም 19 ዓመቷ ላይ ነበረች። ጊዜው ደግሞ በሰላም ማስከበር ሂደት ውስጥ ተሳታፊ የሆነችበት ነው።

ወጣትነትና የሀገር ፍቅር በሚያንቀለቅለው ወኔ ውስጥ ሆና ከተሰው ሰዎች ላይ ጥይት በመሰብሰብና በማከፋፈል በተሰለፈችበት ግንባር ጀብዱ የፈፀመች ጀግና ሆናለች። ከባድ ተተኳሽ በማንገብም በሽክምም ሆነ በተኩስ መከላከያውን ጭምር አስደምማለች። በተሰማራችበት አውደ ውጊያም ቢሆን መሳሪያ ለጨረሱ ጓደኞቿ መሳሪያ በማቀበል፤ በማስተባበርና በታላቅ ፅናት የታገለች አፍላ ወጣት ነች። ለዚህ ጀግንነቷም የዓለም የሴቶች ቀን በሚከበርበት ወቅት እውቅና አግኝታለች።

ሌላኛዋ ባለታሪካችን ምክትል አስር አለቃ ሂሩት አዲሱ ስትሆን፤ በአስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ የተፋላሚውን ምሽግ ለመስበር በሚያደርገው ትንቅንቅ ላይ የቀኝ እግሯን ስትመታ ህክምናን ሳይሆን ወደፊት መጓዝን መርጣ የቆሰለ እግሯን አስራ በመፋለም አኩሪ ድል የፈጸመች ናት።

ምክትል አስር አለቃ ሂሩት፤ ምሽግ ለማስለቀቅ በሚደረግ ፍልሚያ ላይ ተራራውን ወደ ላይ እየወጣች በምትፋለምበት ወቅት ነበር እግሯ ላይ ጉዳት የደረሰው። ነገር ግን የሴትነት ድካም ብሎም ቁስለኝነት ሳያግዳት ለቆመችለት አላማ ሞትን መርጣ እግሯን በጨርቅ አስራ መፋለሟን ቀጠለች። በብዙ ጀብድም ጉዞዋን አጠናቀቀች። ለዚህ ደግሞ ጀግና በመባል እውቅና ማግኘት ችላለች።

የሴቶቻችን አኩሪ ገድል ተተርኮ የሚያልቅ አይደለምና ስንቀጥል የምናገኛት አስር አለቃ ኑሪያ አወልን ነው። እርሷም እንደሌሎቹ ጀግና ተብላ ከተሸለሙትና እውቅና ከአገኙት መካከል ነች። እንዴትና ለምን አገኘች ከተባለ አስር አለቃ ኑሪያ ሰሜን እዝ ላይ በግዳጅ ላይ እያለች ነበር ለአንድ ተልእኮ ወደ ሌላ ቦታ የተላከችው። እሷ ተመልሳ እንደመጣች ስለሆነው ነገር ምንም አይነት መረጃ አልነበራትም። በዚህም የመሳሪያ ዲፖ ላይ የጥበቃ ስራዋን መከወን ጀመረች። ነገር ግን የጠበቀችው ነገር አልነበረም የሆነው። ድንገት ከየት እንደ መጣ የማታውቀው አካል አፈናት፤ መሳሪያዋን ማስረከብ እንዳለባትም ነገራት።

እርሷ ግን ‹‹ ፈርሜ የተቀበልኩትን መሳሪያ ለማንም አልሰጥም፣ ከምትኩም ከነመሳሪያዬ እሞታለሁ፤ ለሀገር መሞት ክብር ነው።›› በማለት ጥያቄያቸውን አልተቀበለቻቸውም። ይልቁንም እዛው በፅናት በመጠበቅ ነፃ እስኪወጣ ድረስ ታግላለች። ከነጻነት በኋላም በተለያዩ ግዳጆች ላይ ተሰልፋ በብቃት የተወጣች ጀግና ነች። በጦር



ሜዳ ላይ እያለችም አዛዧ በጥይት ተመትቶ ከፊቷ ሲወድቅ እሱን ከነትጥቁ ተሸክማ ያለምንም ድካም እስከወገን ጦር ድረስ ለማድረስ በጣም ከፍተኛ ፈተናዎችን አሳልፋለች። አዛዧ ሕይወቱ ሳይተርፍ ቢቀርም በጥንካሬና ፅናቷ ግን ሁሉም የሚተማመንባት ሆናለች።

በራሷ ተነሳሽነት ከአንድ ቦታ ወደ ሌላ ቦታ መሳሪያ በማጓጓዝ፤ ግዳጁን በብቃት በመወጣት፤ ስለሀገር ሲሉ የወደቁትን በመርዳት፤ ውሃ ለምና ውጊያው እንዳይቋረጥ በማጠጣት ጀብዱ የፈፀመችው ደግሞ ጀግናዋ አስር አለቃ ፀጋነሽ ያጎም አንዷ መከላከያ ካፈራቸው ጀግኖች መካከል የምትጠቀስ ናት።

ሌላኛዋ ጀግና መሰረታዊ ወታደር ወይንሸት ነገአ ስትሆን፤ ስርቃ በሚባል ቦታ አንድ ምሽግ ውስጥ ሆና የሰራዊቱን እንቅስቃሴ በከባድ ተኩስ ሲያስቆም የነበረን ወታደር አነጣጥራ በመምታት ሕይወቷን ለአደጋ አጋልጣ ሌሎችን የታደገች ጀግና ነች።

ከውጊያው ባሻገር በኢትዮጵያ መከላከያ ሰራዊት ውስጥ ሆነው ሌሎች ተግባራትን ከሚፈጽሙ መካከል ብርጋዴር ጀኔራል እርጎ ሺበሺ አንዷ ናት። መከላከያ ሰራዊትን የተቀላቀለችው በ1982 ዓ.ም ሲሆን፤ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ እንደ ሴትም እንደ ወታደርም የአገርን ዳር ድንበር በመጠበቅ የተቻላትን ሁሉ ስታበረክት የቆየችና አሁንም እያገለገለች ያለች ናት።

ብርጋዴር ጀኔራል እርጎ ሺበሺ አባባል፤ ወታደርነት ብዙ ውጣ ውረድ ያለበት ሙያ ነው። ፈተናውም ለሁለቱም ጾታ ይጠነክራል። ሆኖም ግን በሴቶች ላይ ፈተናው የበለጠ ያይላል። ሆኖም ሙያው ከፈተና ባሻገር ሕይወትን ቀላልና ዘመናዊ አድርጎ ለመምራት የሚያስችል ነው። ምክንያቱም ሙያው በሥነ ምግባር የታነጸ ያደርጋል፣ አገር ወዳድነትን ያላብሳል፣ ለአገር ክብር ዝቅ ማለትን ያስተምራል፤ ጠንክሮ መስራትንና ስኬታማ መሆንን ያረጋግጣል። ስለሆነም ሴቶችም ሆኑ ወንዶች በዚህ መስክ ውስጥ ሲያልፉ እነዚህን ሁሉ በሕይወታቸው ውስጥ ያኖራሉና ወታደርነት ልዩ ነው።

በዓለም አቀፍ የሰላም ማስከበር ታሪክ ሁለተኛዋ አፍሪካዊት ምክትል ኮማንደር ሴት ጀነራል መኮንንና በመከላከያ ሚኒስቴር የበጀትና ፕሮግራም ዳይሬክተር ብርጋዴር ጀነራል ዘውዴ ኪሮስ ሌላኛዋ መከላከያ ሠራዊት ያፈራቸው እንቁ ሴት ሲሆኑ፤ በውትድርናው ዓለም ከ30 ዓመታት በላይ ለአገራቸው ተዋድቀዋል።

እንደ እርሳቸው አገላለጽ፤ በሠራዊቱ ውስጥ ሴቶች በመሆናቸው የተለየ የሚሰጣቸው ግዳጅ የለም። ምክንያቱም ውትድርና የቡድን ሥራ ነው። ስለዚህም ሴቶች በተልዕኮ አፈፃፀምም ከወንዶች እኩል አንዳንዴም ከዛ አለፍ ብለው ይሳተፋሉ። ይህም የሚሳየው ‹‹ሴቶች አይችሉም›› ከሚባል ይልቅ ዕድሉ ከተሰጣቸው በሁሉም የሥራ መስክ ገብተው ውጤታማ ይሆናሉ የሚለውን ነው።

በመጨረሻ ልናነሳቸው የወደድናቸው ጀግነዋ ሴት ሜጀር ጄነራል ጥሩዬ አሰፌን ሲሆን፤ መከላከያ ካፈራቸው ጀግኖች መካከል ይመደባሉ። በልጅነታቸው የጀመሩት የትግል ሕይወት ዛሬ ላይ ከፍ ወዳለ ወታደራዊ ማዕረግ አድርሷቸዋል። በአሁኑ ወቅት በኢትዮጵያ ሶስተኛዋና ብቸኛዋ የሴት ሜጀር ጀነራል እንደሆኑ ይነገርላቸዋል። መከላከያን ሲቀላቀሉ በእድሜያቸው ትንሽ ሲሆኑ፤ እግረኛ ሆነው ሰራዊቱን አገልግለዋል። በዚህም ለመጀመሪያ ጊዜ ምዕራብ አርማጭሆ (ጎንደር) የሚባል ቦታ ላይ ነው ውጊያ የተካፈሉት። ከእግረኛ እንደወጡ የኪነት ቡድኑን ተቀላቅለው በቡድኑ ስራ ህዝባዊ ተሳትፎን መቀስቀስና ታጋዩን ማነቃቃት ጀመሩ።

ቀጣዩ ተግባራቸው ከውጊያ ውጭ ሰራዊቱን የሚደግፉ የህክምና ስራዎች፣ የህትመት ውጤቶችን የማባዛትና የማሰራጨት፣ ትጥቅ ማዘጋጀት፣ የሬዲዮ መገናኛዎች ብልሽት ሲያጋጥማቸው መጠገንና ሌሎች ተግባራትን በሚያቀናጀው ማዕከላዊ ጽህፈት ቤት ውስጥ ጸሐፊ ሆነው ሰርተዋል። ከዛ በኋላ ደግሞ ህትመት ራሱን ችሎ ሲቋቋም የብአዴን ህትመት ክፍል ውስጥ እንዲሰሩ ሆኑ።

ሜጀር ጀነራል ጥሩዬ የሕወሓትን ጦርነት ከቀደመው ጦርነት ጋር ሲያነጻጽሩ እንዲህ ይላሉ። ‹‹ ቀደም ሲል የነበረው ዘመቻ ጠላት ተብሎ የተፈረጀውን የደርግ ሰራዊት ለማስወገድ ነበር ፤ ህዝቡም የዴሞክራሲ የእኩልነት ጥያቄን አንስቶም ስለነበር ጦርነቱም የህዝብ ጥያቄ እንዲመለስ ማድረጊያ ሆኖ አልፏል። አሁን ግን በትግራይ ክልል ያጋጠመን ትንኮሳና ኋላም የተሄደበት የህግ ማስከበር ዘመቻ ከዛኛው ፍጹም የተለየ ነው። ሊነጻጸር የሚችልም አይደለም። ጁንታው ቡድን ያን የሚዘገንን ክህደት የፈጸመው ባሳደጋቸውና በሚመራቸው ልጆቹ ላይ ነው።

ራዕይ እያሳየ፣ እያሰለጠነ፣ ማዕረግ እየሰጠ፣ እየኮተኮተ ያሳደገ አለቃ (አባት) ቢሆንም ከአባት በማይጠበቅ ስነ ምግባር ልጆቹን በተኙበት ጨፍጭፏል። ይህንን የሚያደርገው ደግሞ ጠላት እንጂ በተለያዩ መስኮች አብሮ የተሰለፈ፣ የበላ፣ የጠጣ፣ ከጎንህ የነበረ ሰው ሊሆን አይገባውም ነበር። ነገር ግን ይህንን አድርጎታል። ሆኖም ማሸነፍ እንዳልቻለ አይተነዋል። ምክንያቱም አገር ለእውነት እንጂ ለተንኮል አትንበረከክም። በአገር የመጣ አካልም ቦታ የለውም።››

ቀጥለውም ሕወሓት ጋር ያለው ስሜትም ሆነ ፍላጎት የስልጣን ጥማት ነው ይላሉ። የስልጣን ጥማት ባይሆን ኖሮ አብሯቸው ብዙ መከራን ያየ ላለፉት በርካታ ዓመታት ክልሉንና አገርን ሲጠብቅ ለነበረ ወታደር ይህንን መሰሉን ክህደት ለመፈጸም መነሳሳቱ አይኖርም ነበር ባይ ናቸው።

እንደ እርሳቸው እምነት፤ ሰራዊት ማለት በየትኛውም አገር ላይ አገር ጠባቂ፣ ለአገሩ ክብርና አንድነት የሚሰዋ፣ አካሉን የሚሰጥ፣ ደሙን የሚያፈስ ነው። ይህንን ደግሞ በሕወሓት ዘንድ ማየት አልተቻለም። ምክንያቱም እርሱ ስልጣን እንጂ ሕዝብን አላየም። ራሱን እንጂ አገሩን አላስቀደመም። ለዚህም ነው ባለመረዳት ውስጥ ሆነው ሰራዊቱን ለመግደል የሞከሩት። ይህ ደግሞ ሰራዊት የሌላት አገር አገር ሆና መቀጠል እንደማትችል ስለማያውቁ ያደረጉት ነው። አዎ ሕወሓት የኢትዮጵያ ብቻ ሳይሆን የዓለምም ጠላት እንደሆነ መገንዘብ ያለብን ይመስላል። ምክንያቱም በዓለም ላይ ተፈጽመው የማያውቁ የሰብዓዊ መብት ጥሰቶችን አድርጓል። እናም ውግዘታችን ብቻ ሳይሆን ትግላችን ጭምር ሆኖ እርሱንና ተከታዮቹን ለዘላለም እንዳይኖሩ ማድረግ ላይ መረባረብ ያስፈልገናል በማለት ሀሳባችንን ቋጨን። ሰላም!!

# ማረፊያ

## አዲስ ዘመን ድሮ

ኃይለማርያም ወንድሙ

**ከሰሳሳ ዓመት በፊት የታተሙ ጋዜጦች የዛሬው አዲስ ዘመን ድሮ ዓምዳችን ትኩረት ናቸው። ከመራረጥናቸው ዘገባዎች መካከል አሁን ካስንበት ወቅት ጋር ተመሳሳይነት ያሳቸው ናቸው። በደርግና በወያኔ መካከል የተካሔደው ድርድር፣ ስደተኞችና ከስደት ተመላሾች ስለሚረዱበት ሁኔታ እንዲሁም የዋጋ ንረትን የተመለከቱ ርዕሰ ጉዳዮች በዘገባዎች የተዳሰሱ ናቸው።**

### የሰላም ውይይቱ ተሳታፊ ቡድን ተሰየመ . ተሳታፊዎች ገንቢ ሀሳብ ይዘው እንዲቀርቡ መንግሥታት ጥሪ አቀረቡ

(ኢ.ዜ.አ)፡- በኢትዮጵያ መንግሥትና በተቃዋሚ ቡድኖች መካከል በመጪው ሰኞ ለንደን ላይ ተሳታፊ የሚሆነውን ቡድን የመንግሥት ምክር ቤት ሰየመ።

የሰላም ልዑካን ቡድኑን የሰየመው በጓድ ሌተናል ጄኔራል ተስፋዬ ገብረኪዳን የኢሠፓ ማዕከላዊ ኮሚቴ የፖለቲካ ቢሮ አባልና የኢትዮጵያ ሕዝቦች ዴሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ ምክትል ፕሬዚዳንት ሰብሳቢነት የመንግሥት ምክር ቤት ትናንት ከቀትር በፊት ባደረገው ስብሰባ ነው።

ጓድ ተስፋዬ ዲንቃ የኢሠፓ ማዕከላዊ ኮሚቴ የፖለቲካ ቢሮ ተለዋጭ አባልና ጠቅላይ ሚኒስትር የቡድኑ መሪ እንዲሆኑ በምክር ቤቱ ተሰይመዋል። በሀገራችን ያለው የወቅቱ እጅግ አሳሳቢ ችግር በሰላማዊ መንገድ ለመፍታት የብሔራዊ ሸንጎ 3ኛ አስቸኳይ ጉባኤ ባሳለፈው ውሳኔ መሠረትና እንዲሁም የመንግሥት ምክር ቤት ሰሞኑን የመፍትሔ ሀሳቦችን ጨምሮ ከፍተኛ ትኩረት በመስጠት ከሁሉም በፊት ሰላም ዘንድ ለአፋጣኝ መፍትሔ በሚያደርገው ጥረት ለንደን ላይ የሚደረገው የሰላም ውይይት የተሳካ እንዲሆን በመድረኩ ላይ ተሳትፎ ለሚያደርገው ቡድን አስፈላጊውን መመሪያ ሰጥቷል።

መንግሥትን በመወከል በውይይቱ የሚሳተፈው ቡድን በአሁኑ ጊዜ በሀገራችን ውስጥ የሚደረገው የእርስ በእርስ ጦርነት ቆሞ የሽግግር መንግሥት ይመሠረት ዘንድ ምቹ ሁኔታ ለመፍጠርና ተገቢውን አስተዋፅኦ ለማድረግ የተዘጋጀ መሆኑን የመንግሥት ምክር ቤት ገልጿል።

(ግንቦት 17 ቀን 1983 ከወጣው አዲስ ዘመን )

### ስደተኞችና ከስደት የተመለሱት ስለሚረዱበት ሁኔታ ውይይት ተካሄደ

(ኢ.ዜ.አ)፣ ከሶማሊያ ተፈናቅለው ወደ ኢትዮጵያ የገቡ ስደተኞችና ከሶማሊያ ወደ አገራቸው የተመለሱትን ኢትዮጵያውያንን መርዳት በሚቻልበት ሁኔታ ላይ የተነጋገረ ስብሰባ ትናንት በማዕከላዊ ፕላን ብሔራዊ ኮሚቴ ጽሕፈት ቤት ተካሔዷል ።

ለስደተኞቹ ዕርዳታ የሚደርስበትን ሁኔታ የሚከታተለውና በቅርቡ የተቋቋመው የሶማሊያ ስደተኞች ድጋፍ ሰጪ ከፍተኛ ብሔራዊ ኮሚቴ ባዘጋጀው በዚሁ ስብሰባ ላይ የዓለም አቀፍ እርዳታ ለጋሽ ድርጅቶች ተወካዮች ተካፍለዋል።

ጓድ ሽመልስ አዱኛ የኢሠፓ ማዕከላዊ ኮሚቴ አባል፣ የሠራተኛና ማኅበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴርና የኮሚቴው አስተባባሪ ለተሳታፊዎች ባደረጉት ገለጻ፣ የሶማሊያ ስደተኞችንና ወደ ሀገራቸው የተመለሱትን ኢትዮጵያውያንን ለመርዳት እስካሁን መንግሥት ከተባበሩት መንግሥታት ስደተኞች ጉዳይ ከፍተኛ ኮሚሽነር ጋር በመተባበር ያልተቆጠበ ድጋፍ ሲሰጥ መቆየቱን አውስተው፣ ለተልዕኮው መሳካት የዓለም አቀፍ ኅብረተሰብ ሲያደርግ የነበረውን ትብብር ገልጸዋል።

በአሁኑ ወቅትም በቂ ምግብ ውሃ መጠለያና መድኃኒት ለማቅረብ ከእርዳታ ሰጭ ድርጅቶች ያልተቆጠበ ትብብርና ድጋፍ እንደሚያስፈልግ አመልክተው በተለይም ለዚሁ አቅርቦት የወሳኝነት ሚና ያለው የትራንስፖርት ችግር መቃለልና አፋጣኝ መፍትሔ ማግኘት እንደሚገባው አስረድተዋል።

ቀደም ሲል በተባበሩት መንግሥታት ስደተኞች ጉዳይ ከፍተኛ ኮሚሽነር የአፍሪካ አህጉር ተወካዮች፣ ከአገር ውስጥ ጉዳይ ሚኒስቴር ተወካዮች ጋር በመሆን በሥፍራው ባደረጓቸው ጉብኝቶች የጉዳዩን አሳሳቢነት መጠቆማቸውን ጓድ ሚኒስትሩ ገልጸው፣ ይህን ችግር አፋጣኝ መፍትሔ እንዲያገኝ ዕርዳታ ለጋሽ ድርጅቶች ያላሰለሰ ድጋፍ እንዲሰጡ ጥሪ አቅርበዋል። ከሶማሊያ ፈልሰው ወደ ኢትዮጵያ የገቡ የሶማሊያ ስደተኞች 640 ሺህ ሲሆኑ ወደ አገራቸው የተመለሱት ኢትዮጵያውያን ደግሞ 246 ሺህ ናቸው።

(መጋቢት 17 ቀን 1983 አዲስ ዘመን ጋዜጣ)

### በዋጋ ንረትና ሥርጭት መዛባት ጉዳይ ላይ ውይይት ተካሄደ

(ኢ.ዜ.አ)፣ ሀገራችን አሁን የምትገኝበት እጅግ አሳሳቢ ወቅት በአዲስ አበባ ከተማ በተከሰተው የዋጋ ንረትና የሥርጭት መዛባት ጉዳይ ላይ በንግዱ ዘርፍ ከተሰማራው ኅብረተሰብ ጋር ተወያይቶ የጋራ ግንዛቤ ለመውሰድና መፍትሔ ለመፈለግ የሚያስችል ስብሰባ ትናንት ተካሂዷል።

ጓድ ግዛው ንጉሤ የአዲስ አበባ አካባቢ ዋና አስተዳደር በዚሁ ስብሰባ ላይ ባደረጉት ንግግር ፤ ወያኔ አገርን ለመከፋፈል በየአካባቢው በከፈተው ጦርነት ምክንያት የተናጋው የኅብረተሰቡ ሰላምና አንድነት ለማስከበር ከፍተኛ እንቅስቃሴ በሚያካሂድበት በአሁኑ ወቅት ነጋዴው በምርቶችና ሸቀጦች ላይ ዋጋ ከመጨመር እንዲቆጠብ አሳስበዋል።

መንግሥት የንግዱ ኢኮኖሚ መስክ ከጊዜ ወደ ጊዜ በተሻለ ሁኔታ እንዲደራጅ፣ እንዲመራና ለአጠቃላይ ኅብረተሰብም ሆነ በዘርፉ ለተሰማራው ዜጋ የተሻለ ጥቅም እንዲሰጥ ለማድረግ የሚቻለው ሁሉ ጥረት ሲያደርግ መቆየቱን ጓድ ግዛው ጠቅሰው፣ ከየወቅቱ ፍላጐትና በተጨባጭ ሁኔታ ጋር ተስማሚ የሚሆኑ ፖሊሲዎችን፣ ሕጎችን፣ መመሪያዎችንና ደንቦችን አውጥቶ ሥራ ላይ በማዋል ንግዱ ከግብታዊነት ተላቆ የተሻለ ሥርዓት እንዲይዝ ጥረት ሲደረግ መቆየቱን አስረድተዋል።

(መጋቢት 24 ቀን 1983 አዲስ ዘመን ጋዜጣ)

### ደን የጨፈጨፉ ተቀጡ

ነገሌ፣ (ኢ.ዜ.አ) በቦረና አስተዳደር አካባቢ ደን ጨፍጭፈዋል ተብለው የተከሰሱ ግለሰቦች እያንዳንዳቸው አንድ ዓመት ጽኑ እሥራት እንዲቀጡ የሊበን አውራጃ ፍርድ ቤት ሰሞኑን ፈርዶባቸዋል።

ዶዩ ጐዳና፣ ዶቶ ጠዲቻና ካሰዬ በኩቲ የተባሉት ግለሰቦች በማንኩሳ ቀበሌ የሚገኘውን ደን በሕገወጥ መንገድ ጨፍጭፈው ለሽያጭ ሲያዘጋጁ እጅ ከፍንጅ ተይዘዋል።

ተከሳሾቹ ጥፋታቸው በበቂ ማስረጃ የተረጋገጠ በመሆኑ እንዳንዳቸው በአንድ ዓመት እሥራት እንዲቀጡና ለሽያጭ የተዘጋጀው የተጠረበ የማዕዘን እንጨትም ለመንግሥት በውርስ ገቢ እንዲሆን በተጨማሪ ወስኗል።

(ግንቦት 10 ቀን 1983 ከወጣው አዲስ ዘመን ጋዜጣ )

# ዓለም አቀፍ



ፕሬዚዳንት ናና አኩፎ-አዶ

## አስከፊው የጋና ኢኮኖሚ ቀውስ

የጋናው ፕሬዚዳንት ናና አኩፎ-አዶ እሁድ እለት ባደረጉት ንግግር "ችግር ውስጥ ነን፤ ይህን ስናገር አላጋነንኩም፣ ብዙ ተንኮል አዘል ሃይሎች በአንድ ጊዜ ሲሰባሰቡ በታሪክ ምሳሌ ላገኝ አልቻልኩም" ብለዋል።

ሲዲ የሚባለው የአገሪቱ መገበያያ ገንዘብ በዚህ ዓመት ከአሜሪካ ዶላር አንጻር የምንዛሪው ዋጋ ከ 50 በመቶ በላይ በመቀነሱ በዓለም እጅግ በጣም መጥፎ አፈጻጸም ካስመዘገቡት ገንዘቦች ተርታ ተመድቧል።

ፕሬዚዳንት አኩፎ አዶ ፣ ለሲዲ ዋጋ መውረድና ለዋጋ ንረቱ ሕገ-ወጥ የገንዘብ አዘዋዋሪዎችን ተጠያቂ አድርገው፣ የአገሪቱ ማዕከላዊ ባንክም ወንጀለኞቹን እንደሚቆጣጠር ተናግረዋል።

የዓለም የነዳጅ ዋጋ መጨመሩ ጋር ተያይዞ በአገሪቱ በተፈጠረው የነዳጅ ዋጋ ጭማሪ ምክንያት የዋጋ ግሽበት ወደ 37 ነጥ 2 በመቶ ከፍ ብሏል። ቀውሱን ለመቅረፍ ብዙ እርምጃዎች እየተወሰዱ መሆናቸውንና በተለይ የፕሬዚዳንቱ፣ የምክትል ፕሬዚዳንቱ፣ የሚኒስትሮች እና የሌሎች የመንግሥት ተሿሚዎች ደሞዝ ላይ 30 በመቶ ቅናሽ እንደሚደረግም ፕሬዚዳንቱ ተናግረዋል።

ጋና ከቀውሱ ለመውጣት በአሁኑ ጊዜ ከዓለም አቀፉ የገንዘብ ተቋም ከአይ ኤም ኤፍ የ3 ቢሊዮን ዶላር የእርዳታ መርሃ ግብር ተጠቃሚ ለመሆን እየተደራደረች ትገኛለች። ፕሬዚዳንቱ በመንግሥት የግምጃ ቤት ሂሳቦች እና ሌሎች የፋይናንስ ሰነዶች ላይ ያሉ ባለሀብቶች በስምምነቱ ምክንያት ገንዘባቸውን እንደማያጡ አረጋግጠዋል።

በኮኮዋና በወርቅ ምርት የምትታወቀው የምዕራባዊቷ አፍሪካ አገር በብድር ጫና፣ ከኮሮና ወረርሽኝ በሩሲያ-ዩክሬን ጦርነት ተደምረው አጣብቂኝ ውስጥ አስገብተታል። በእርግጥ አገሪቱ በማኑፋክቸሪንግ፣ በዓሳ ምርትና በትምህርት ዘርፍ አገልግሎት የተሻለ እድገት ብታስመዘግብም አሁን ከገጠማት የኢኮኖሚ ቀውስ ሊያድኗት አልቻሉም።

## በሞቃዲሾው የቦምብ ጥቃቶች የሟቾች ቁጥር 120 መድረሱ ተነገረ



ጥቃቶቹ የተፈጸሙበት አካባቢ

በሶማሊያ መዲና ሞቃዲሾ በተፈጸሙ ሁለት የቦምብ ጥቃቶች የሟቾች ቁጥር 120 መድረሱን የአገሪቱ ፕሬዚዳንት ሐሰን ሼይክ መሐሙድ መግለጻቸውን ቢቢሲ ዘግቧል።

በእለቱ ቅዳሜ የሰዎች እንቅስቃሴ በሚበዛበት ቦታ መኪና ላይ የተጠመዱ ሁለት ቦምቦች ፈንድተው ከ100 በላይ ሰዎችን ገድለው ከ300 በላይ ማቁሰሉ ተገልጿል።

ጥቃቶቹ የአገሪቱን የትምህርት ሚኒስቴርን ዒላማ ያደረጉ ሲሆን በጥቃቱ ጀርባ የሽብር ቡድኑ አል-ሸባብ እንዳለ ፕሬዚዳንቱ ተናግረዋል።

ፕሬዚዳንት ሐሰን፣ በጥቃቶቹ ከተገደሉት መካከል "በእናቶቻቸው እቅፍ ላይ የበሩ ሕጻናት ይገኙበታል" ማለታቸውን የፈረንሳዩ የዜና ወኪል አመላክቷል።

ፕሬዚዳንቱ በጥቃቱ የተጎዱ 300 ሰዎችን ለማከም ዓለም አቀፍ ትብብርን በመጠየቃቸው የዓለም ጤና ድርጅት ለፕሬዚዳንቱ ጥሪ ምላሽ መስጠቱ ተነግሯል።

በአሁኑ ወቅት ሰፊውን መካከለኛ እና ደቡባዊ ሶማሊያ ተቆጣጥሮ ያለው የጂሃዲስት ቡድኑም በድረ-ገጹ አማካይነት ለጥቃቱ ኃላፊነት እንደሚወስድ አስነብቧል።

ከአል-ቃይዳ ጋር ትስስር ያለው አል-ሸባብ ከሶማሊያ ፌዴራል መንግሥት ጋር ለበርካታ ዓመታት የዘለቀ ጦርነት ውስጥ ይገኛል።

በቅርቡ ወደ ሥልጣን የመጡት ፕሬዚዳንት ሐሰን ሼይክ መሐሙድ ይህ ቡድን ሰኔ 2014 ዓ.ም ሞቃዲሾ በሚገኝ ዝነኛ ሆቴል ላይ ጥቃት አድርሶ 21 ሰዎች ከተገደሉ በኋላ በአል-ሸባብ ላይ መጠነ ሰፊ ኦፕሬሽን ማዘዛቸው ይታወሳል።

ከትናንት በስቲያ ቅዳሜ ያጋጠሙት ሁለቱ ፍንዳታዎች የተፈጸሙት በጥቂት ደቂቃዎች ልዩነት ነበር። መኪና ላይ ተጠምደው የነበሩት ቦምቦች ፍንድተው በአካባቢዎች የነበሩ ሕንጻዎችን እና ተሽከርካሪዎችን አውድመዋል።

የመጀመሪያው ፍንዳታ የትምህርት ሚኒስቴርን የመታ ሲሆን ሁለተኛው ፍንዳታ ደግሞ የደረሰው የአደጋ ጊዜ ሠራተኞች በፍንዳታው ቦታ እንደደረሱ መሆኑን ሮይተርስ የዜና ወኪል ዘግቧል።

ከአምስት ዓመት በፊት በዚሁ ቦታ ላይ ከባድ መኪና ላይ የተጠመደ ቦምብ ፈንድቶ 500 ሰዎች ተገድለው ነበር። ይህ ጥቃት በአገሪቱ ታሪክ በርካታ ሰዎችን የገደለ ሆኖ ተመዝግቧል።

ጥቃቶቹ ካጋጠሙ በኋላ ቤተሰብ የጠፋቸው በመቶዎች የሚቆጠሩ ሰዎች ፍንዳታዎቹ ባጋጠሙባቸው ቦታዎች ሰዎችን ሲፈልጉ ታይተዋል።

ከሟቾቹ መካከል አንድ አውቀ ጋዜጠኛ እና ከፍተኛ የፖሊስ መኮንን እንደሚገኙበት ተገልጿል።

አሜሪካ፣ ቱርክ፣ ኳታር እና ጀርመን ጥቃቱን አውግዘዋል። የአፍሪካ ኅብረት ደግሞ ይህ ጥቃት አል-ሸባብን ለማጥፋት ወታደራዊ እርምጃው ተጠናክሮ መቀጠል እንዳለበት የሚያሳይ ነው ብሏል።

አል-ሸባብ በአፍሪካ ኅብረት የሚደገፈውን የሶማሊያ መንግሥት ገርስሶ ሥልጣን ለመያዝ ባለፉት 15 ዓመታት ሲዋጋ ቆይቷል።

The Ethiopian Herald
አዲስ ዘመን
BARIISAA
العلم
ወጋሕታ
BAKKALCHO
የህትመት ውጤቶቻችንን ለማንበብ ድረገጾቻችንንና ፌስቡክ ገጾችንን ይጎብኙ!
የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት
ዌብሳይት፡- www.press.et
ፌስቡክ፡- Ehiopian Press Agency



ይህ ቦታ
ለማስታወቂያ ክፍት ነው!

# ከ20 ዓመት በታች ብሔራዊ ቡድን ነገ የመጀመሪያ ጨዋታውን ያደርጋል

**ብርሃን ፈይሳ**

በቀጣዩ የፈረንጆቹ ዓመት ለሚካሄደው ከ20 ዓመት በታች የአፍሪካ ዋንጫ ተሳታፊ የሚሆኑ ቡድኖችን ለመለየት ከሚካሄዱ የማጣሪያ ጨዋታዎች መካከል አንዱ የምስራቅና መካከለኛው አፍሪካ እግር ኳስ ማህበር (ሴካፋ) የሚያሰናዳው ውድድር ነው። ዘንድሮም ይህ ውድድር ለ14ኛ ጊዜ በሱዳን አስተናጋጅነት ከቀናት በፊት መካሄድ መጀመሩ ይታወሳል። የዚህ ውድድር ተካፋይ ከሆኑ አገራት መካከል አንዱ የሆነው የኢትዮጵያ ከ20 ዓመት በታች ብሄራዊ ቡድንም ነገ የመጀመሪያ ጨዋታውን የሚያከናውን ይሆናል።

በሱዳን አዘጋጅነት ሰባት አገራት የሚካፈሉበት ይህ ውድድር በአል ሂላል ስታዲየም ከተጀመረ ቀናትን ያስቆጠረ ሲሆን፤ በምድብ አንድ የተደለደሉ አገራት የመጀመሪያ ጨዋታቸውን ማከናወን ችለዋል። በዚህም መሰረት የውድድሩ አዘጋጅ የሆነችው ሱዳን ከደቡብ ሱዳን ጋር ያለ ግብ መለያየት ችለዋል። በብሩንዲ እና ጅቡቲ መካከል የተካሄደው ጨዋታ ደግሞ በብሩንዲ የ5 ለምንም ሰፊ የግብ ልዩነት ሊጠናቀቅ ችሏል። በዚህ ጨዋታ አርተር ኒቢኮራ የተባለው ተጫዋች ሶስት ግቦች በማስቆጠር ቀዳሚው ተጫዋች ለመሆንም ችሏል።

በምድብ ሁለት ኢትዮጵያ፣ ታንዛኒያ እና ኡጋንዳ ሲደለደሉ፤ ኢትዮጵያ ከታንዛኒያ ጋር የመጀመሪያውን ጨዋታ ነገ የምታካሂድ ይሆናል። በቀጣይ ደግሞ ካለፈው ዓመት የሴካፋ አሸናፊው ዩጋንዳ ብሄራዊ ቡድን ጋር የሚገናኝ ይሆናል። በአሰልጣኝ እድሉ ደረጀ የሚራው ወጣት ቡድኑ ከተያዘው ወር የመጀመሪያ ቀናት አንስቶ ወደ ዝግጅት የገባ ሲሆን፤ ተጫዋቾቹ ከውድድር የተሰባሰቡ እንደመሆኑ በታክቲክ እና የፍጥነት ስራዎች ላይ አተኩሮ ዝግጅት ሲያደርግ


የኢትዮጵያ ከ20 ዓመት በታች ብሔራዊ ቡድን በሱዳን ዝግጅቱን አጠናክሮ ቀጥሏል፤

ቆይቷል። በተለይ የአሸናፊነት ስነልቦናን እንዲላበሱም በአሰልጣኞች ቡድን በትኩረት የተሰራበት መሆኑንም አሰልጣኙ ጋዜጣዊ መግለጫ በሰጡበት ወቅት አሳውቀዋል። በኢትዮጵያ ስፖርት አካዳሚ ልምምድ ሲያደርግ የቆየው ቡድኑ ያለበትን አቋም ለመለካትም ከመቻል ከ20 ዓመት በታች ቡድን ጋር ተጫውቶ 3ለ0 በሆነ ውጤት ነበር ያሸነፈው።

የኢትዮጵያ እግር ኳስ ፌዴሬሽን ፕሬዚዳንት አቶ ኢሳያስ ጅራ እና ዋና ጸሀፊው አቶ ባህሩ ጥላሁን፤ ቡድኑ ወደ ሱዳን ከማቅናቱ አስቀድሞ ልምምዱን በሚያከናውንበት ስፍራ ተገኝተው ልምምዱን ተከታትለዋል። አቶ ኢሳያስ ባደረጉት ንግግርም፤ ይህ ውድድር ለአፍሪካ ዋንጫ አቋራጭ የሆነ ውድድር ነው፤ በመሆኑም ይህንን ዕድል መጠቀም አስፈላጊ መሆኑን ጠቁመዋል። ቡድኑ ያለበት ምድብ ከዞኑ ጠንካራ አገራት ጋር በመሆኑ ትኩረት ሰጥቶ በመጫወትና ጥቂት ጨዋታዎችን በአሸናፊነት መወጣት በግብጽ አስተናጋጅነት ለሚደረገው የአፍሪካ ዋንጫ ለማለፍ መልካም አጋጣሚ በመሆኑና አጋጣሚውን በአግባቡ መጠቀም እንደሚያስፈልግም ገልጸዋል። በመጨረሻም ለቡድኑ አባላት መልካም እድል እንዲገጥማቸው ተመኝተዋል።

ቡድኑ ባለፈው እሁድ ጥቅምት 20/2015 ዓ.ም ወደ ሱዳን የተጓዘ ሲሆን፤ አመሻሽ ላይም ልምምድ መጀመሩን የኢትዮጵያ እግር ኳስ ፌዴሬሽን አሳውቋል። የወጣት ብሄራዊ ቡድኑ አሰልጣኝ እድሉ የዛሬውን ጨዋታ አስመልክቶም፤ የመጀመሪያ ጨዋታ ወሳኝ መሆኑን ይገልጻሉ። ቡድኑ ከታንዛኒያ ጋር የሚኖረው ጨዋታ የማለፍና ያለማለፍ እድሉን የሚያሰፋ እንደመሆኑ ቡድኑ ትኩረት አድርጎ ይጫወታል። ከሌሎች የብሄራዊ ቡድን ጨዋታዎች ይህንን መረዳት በመቻሉ ቡድኑ በዛሬው ጨዋታ አሸንፎ ለመውጣት ማቀዱንም አሰልጣኙ አመላክተዋል።

Ethiopian Cooperative Commission

ከኢትዮጵያ ኅብረት ሥራ ኮሚሽን ጋር በመተባበር
በየሰምንቱ የሚታተም

# «የቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማኅበራት ለተጠናከረ የፋይናንስ አቅም»

**በአስምነህ ቸርነት**

የፋይናንስ ተደራሽነት፣ ተጠቃሚነትና አካታችነትን ለግብርና ልማትና ግብይት መዘመንና መስፋፋት እንዲሁም ወጣቶችና ሴቶች በተለያዩ አዋጭ የስራ ዘርፎች ውስጥ ገብተው ከድህነት እንዲላቀቁ ለማስቻል ወሳኝ ዘርፍ ነው። በአሁኑ ጊዜ ኢትዮጵያን ጨምሮ በርካታ የአፍሪካ አገራት የፋይናንስ አካታችነትን እንደ አንድ አገራዊ ስትራቴጂ አድርገው እየወሰዱት ነው። በዚህም መሰረት በአገራችን የብሔራዊ የፋይናንስ አካታችነት ስትራቴጂ በ2010 ይፋ ተደርጎ ወደ ተግባር ምዕራፍ ከተገባ በኋላ ተስፋ ፈንጣቂ ለውጦች ታይተዋል።

ለአብነት ያህል አገራችን ኢትዮጵያ ዓለምአቀፍ የዲጂታል ሽግግር አካል በመሆን እ.ኤ.አ በ2025 የዲጂታል ትራንስፎርሜሽን ስትራቴጂን ሙሉ በሙሉ ለመተግበር በቁርጠኝነት በመስራት ላይ ትገኛለች። ከገንዘብ ፖሊሲ አኳያም አገራዊ የምርት ዋጋ ሁኔታ የተረጋጋ እንዲሆን የተለያዩ የገንዘብ ፖሊሲ መሣሪያዎች ተግባራዊ ተደርገዋል። የገንዘብ ዕድገትን በመቆጣጠር የገንዘብ አቅርቦት ዕድገት ከጠቅላላ የአገር ውስጥ ምርት ዕድገት (ጂ.ዲ.ፒ) ጋር የተመጣጠነ እንዲሆን ያላሰለሰ ጥረቶች እየተደረጉ ናቸው።

በአገራችን የፋይናንስ አካታችነትን ለማሳደግ በርካታ ጥረቶች እየተደረጉ ቢሆንም ሰፊ የማህበረሰቡ ክፍል ተደራሽ ከማድረግ አንጻር ገና ብዙ ርቀት ይቀረናል። በአሁኑ ግዜ በአገራችን በባንክና በሌሎች መደበኛ የፋይናንስ ተቋማት የሂሳብ ደፍተር ከፍተው የሚጠቀሙ አዋቂ ሰዎች ቁጥር ገና ከ35 በመቶ አላለፈም።

በመሆኑም የፋይናንስ አካታችነትን ለማሳደግ ዘላቂ የፋይናንስ ልማት ላይ መስራት አስፈላጊ ነው። በዚህ ረገድ በአገራችን የገንዘብ ቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበራት በመደበኛ ባንክ ተደራሽ ያልሆነውን የኅብረተሰብ ክፍል ባንክን ተክተው ኅብረተሰቡ በሚኖርበት አቅራቢያ አገልግሎት የሚሰጡ አማራጭ ህዝባዊ የፋይናንስ ተቋማት በመሆን እያገለገሉ ይገኛሉ።

በ2014 በጀት ዓመት ሪፖርት መሰረት በአገራችን 22 ሺ 485 የገንዘብ ቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበራት፣ 133 የገንዘብ ቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ዩኒየኖችና ሁለት የገንዘብ ቁጠባና ብድር ኅብረት ስራ ፌዴሬሽኖች በሁሉም ክልሎችና የከተማ አስተዳደሮች ተቋቁመው ከስድስት ሚሊዮን 916 ሺ 853 በላይ አባላት ማፍራትና ከ 36 ቢሊዮን 983 ሚሊዮን 896 ሺ 865 ብር በላይ ቁጠባና ዕጣ ማሰባሰብ ችለዋል። በ2014 በጀት ዓመት ብቻ ዘጠኝ ቢሊዮን ብር የብድር ስርጭት አከናውነዋል።

በዚህም ጥረት በርካታ አባላት ወደ ግብርና ዘርፍ፣ ንግድ ስራ፣ ትራንስፖርት አገልግሎትና ወደ ሌሎች የገቢ ማስገኛ ፕሮግራሞች ገብተው ለራሳቸውና ለሌሎች የስራ ዕድል መፍጠርና ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ችግሮቻቸውን መቅረፍ ችለዋል። በከተማ አካባቢ የሚስተዋለውን የመኖሪያ ቤት ችግር ከማቃለል አኳያም አባላት እየቆጠቡ የቤት ባለቤት እንዲሆኑ የቁጠባና ብድር ኅብረት ስራ ማህበራት የራሳቸውን ሚና ተጫውተዋል። እንዲሁም በህጻናት የቁጠባ አገልግሎት ህጻናት የቁጠባ ባህልን ተላብሰውና የይቻላል አስተሳሰብን አጎልብተው እንዲያድጉ ትውልድን በመቅረጽ ረገድ የድርሻቸውን እየተወጡ ናቸው።

ሆኖም ግን በአገራችን ተደራጅተው አገልግሎት በመስጠት ላይ ያሉ የገንዘብ ቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበራት ቁጠባን በስፋት ከማሰባሰብ፣ ተደራሽነትን በሁሉም አካባቢ ከማስፋፋትና የተደራጀና የተቀላጠፈ የፋይናንስ አገልግሎት ከመስጠት አንጻር ውስንነት አለባቸው። ስለሆነም ኅብረት ስራ ማኅበራቱ አገራችን የተለመቻቸውን የልማት ግቦች እንዲያሳኩ አስተማማኝና አማራጭ የፋይናንስ ምንጮች ሆነው ለማገልገል የአገር ውስጥ የቁጠባ ባህልን ማሳደግ፣ የአገር ውስጥ ገቢን ማሳደግና ማስፋፋትና የፋይናንስ ምርታማነትን ማሻሻል ይጠበቅባቸዋል። የፋይናንስ አቅሞችን ከጊዜያዊነት ይልቅ ዘላቂና ጥራት ወዳላቸው ምንጮች ለማሸጋገር ደግሞ የተለያዩ የፋይናንስ አገልግሎት ምርቶች በማስፋት ተወዳዳሪነታቸውን ማጎልበትና ዘመናዊ የመረጃ ቴክኖሎጂ ስርዓት በመዘርጋት ፈጣንና ቀልጣፋ አገልግሎት ለመስጠት የሚያስችል አቅም መገንባት ላይ በትኩረት መስራት ይኖርባቸዋል።

ዘንድሮ በአገር አቀፍ ደረጃ ለመጀመሪያ ጊዜ እና በዓለም አቀፍ ደረጃ ለ74ኛ ግዜ “Empower Your Financial Future with a Credit Union” “የቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማኅበራት ለተጠናከረ የፋይናንስ አቅም” በሚል መሪ ቃል ጥቅምት 21 ቀን ተከብሮ ውሏል። ዓለም አቀፍ የቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበራት ቀን እ.ኤ.አ. ከ1948 ዓ.ም ጀምሮ በየዓመቱ በወርሃ ጥቅምት የሚከበር ነው። የዚህ ክብረ በዓል ዓላማ የቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማኅበራት በዓለም ዙሪያ እያከናወኗቸው ስላለው ታላቅ ስራ ግንዛቤን ለማስጨበጥና አባላት በዘርፉ የበለጠ እንዲሰማሩ እድል ለመስጠት ነው።

በዚህም መሰረት ዕለቱ በሴክተሩ ያሉ ችግሮችን ለመፍታት የአገራችንም ሆነ የዓለም የገንዘብ ቁጠባና ብድር ኅብረት ስራ ማህበራት የደረሱበትን የዕድገት ደረጃና በዘርፉ የተገኙ ውጤቶችና ተሞክሮችን በመለዋወጥ፣ ስለ ዘርፉ አስፈላጊነት፣ ጠቀሜታ፣ ፋይዳና ስኬቶች አስመልክቶ ለፖሊሲ አውጪዎች፣ ለዘርፉ ምሁራንና ለመላው ህብረተሰብ ግንዛቤ በማስጨበጥ ተከብሯል። በዕለቱም የፌዴራልና ክልል የመንግስት ከፍተኛ ኃላፊዎች፣ የፌዴራልና የክልል የኅብረት ሥራ አደራጅና ማስፋፊያ አካላት፣ የገንዘብ ቁጠባና ብድር ኅብረት ስራ ማህበራት ሊቀ መናብርቶችና ሥራ አስኪያጆች፣ የኅብረት ስራ ማኅበራት አቅም ገንቢ አካላትና ተወካዮች፣ የሚዲያ አካላትና ጥሪ የተደረገላችሁ እንግዶች ተገኝተዋል።

የገንዘብ ቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበራት አባላት ኢኮኖሚያዊ ፍላጎቶቻቸውን ለማሟላት ያቋቋሟቸውና በአባላት ባለቤትነት የሚተዳደሩ የፋይናንስ ተቋማት ናቸው። ሰዎች በቁጠባ መልክ ገንዘብ አሰባስበው በቀላሉ ብድር በመውሰድ የራሳቸውን ዓላማ የሚያሳኩባቸው ናቸው። እነዚህ የገንዘብ ቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበራት በአሁኑ ጊዜ የተለያዩ የፋይናንስ አገልግሎት ፕሮዳክቶችን ለአባላት ተደራሽ እያደረጉ ሲሆን በቁጠባ አገልግሎት መደበኛ፣ መደበኛ ያልሆነ፣ የጊዜ ገደብ፣ ተንቀሳቃሽ፣ የውል፣ የክብረ በዓል፣ የልጆች ቁጠባና ሌሎች የቁጠባ አይነቶች እያቀረቡ ነው። በብድር አገልግሎት (በአጭርና መካከለኛ) ለግብርና፣ ለንግድ፣ ለግንባታ፣ ለዕደ ጥበብ፣ ለትራንስፖርትና ለሌሎች ተግባራት ብድር እየሰጡ ነው። እንዲሁም ለአነስተኛ የመድህን ሽፋን አገልግሎት እያቀረቡ ይገኛሉ።

አድራሻ | የፌዴራል ኅብረት ሥራ ኮሚሽን | 0115573448/ 0118592105 | ፖ.ሳ.ቁ. 19787 | Facebook: Federal cooperative Agency | Website: www.fca.gov.et

በብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት ታተመ